# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
# ጤና ቢሮ

# የጤና ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ማንዋል

ቁጥር 057/2013

ሚያዝያ 2002

# ማ□ሁ□

□□


1. የጤና ክብካቤ ጥራት ትርጓሜ ........................................ 3

2. በጤና ተቋማት ውስጥ ጥራትን ለማሻሻል የተለዩና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ተግባራት .............. 6

3. የውስጥ ገቢን ተጠቅሞ ጥራትን ለማሻሻል ቅድሚያ የሚሰጣቸው ተግባራት .................. 10

4. የጥራት ማሻሻያ ተግባር ዕቅድና አፈጻጸም ................................. 13

ክፍል አምስት................................................ 16

5. የውስጥ ገቢን ለማጠቀም የተፈቀዱ የሥራ ዝርዝሮች ........................... 16

6. ክትትልና ግምገማ ............................................ 23

6.1 የአፈጻጸም ክትትል ......................................... 24

6.2 ግምገማ................................................ 25

7. አባሪዎች..........................................................27

7.1 ዕዝል አንድ.............................................. 27

7.2. ዕዝል ሁለት ............................................. 35

7.3 ዕዝል ሶስት ............................................. 43

## ክፍል አንድ
## 1. የጤና ክብካቤ ጥራት ትርጓሜ

ምንም እንኳን አንድ ወጥ የሆነ ትርጉም ለማስጠት አስቸጋሪ እንደሆነ ቢታመንም በተለያዩ ማስክ ባሉ ፀሐፊዎች የተለዩ ትርጉሞች ጥቅም ላይ እንደዋሉ ሚጃዎች ያማለክታሉ፡፡ አቬዲስ ደናቤዶይን ኤም.ዲ 1980 በሰጠው ትርጉም ማሰረት የጤና አገልግሉት የተለያዩ ቴክኒኮችንና መሣሪያዎችን በማጠቀም ላይ የተማሰረተ እንደሚሆኑ ጥራቱ የሚዛነው በማስኩ ያለውን የሳይንስ እውቀት፣ ያሉ ቴክኖሎጂዎችን አጠቃቀምና ሊገኝ የሚባውን ጥቅም ሊደርስ ከሚባ ተዛማጅ ችግር አንጻር በማጻጸር በልጦ ሲገኝ ነው ይላል፡፡ በዚህ ማበራሪያ ማሰረት የጥራት ደረጃ የሚወሰነው በሚሰጠው የጤና አገልግሎት ረገድ ልናገኝ ያሰብነው ጥቅምና ሊከሰት በሚችል ያልታሰበ ችግር/ሪስክ/ መካከል በምንፈልገው ዓይነት ሚዛናዊ ወጤት ሲገኝ ነው፡፡

ኤም.አይ.ሮኢሚር እና ሞንቶሮ አጉይለር ከዓለም የጤና ድርጅት በግሪጎሪያን አቆጣጠር በ1988 በቀረበው የትርጉም ማበራራያ ማሰረት ጥራት ያለው ጤና ክብካቤ ደረጃውን ጠበቆና ምንም ችግር የለበትም ተብሎ ታምኖበት በትክክል የሚተገበር፣ በማስጠት ላይ ያለው ጤና አገልግሉት በሚጠቃው ህብረተሰብ አቅም ተደራሽ የሆነ እና እንዲሁም አገልግሎት እየተሰጠ ባለበት ህብረተሰብ ማሃል በሞት፣ በታሞ መተኛት፣ አካል ጉዳተኝነት እና ባልተመጣጠነ ምግብ ችግር ዙሪያ በሚታዩ ችግሮች ላይ ተጨባጭ ለወጥ ማምጣት የቻለ እንደሆነ ጥራቱን የጠበቀ ጤና ክብካቤ ሊባል ይችላል፡፡

ሌላው ጥራት ባለው ጤና ክብካቤ ትርጉም ዙሪያ በቀረበው አሜሪካ ማበራሪያ ማሰረት ደግሞ ጥራት ያለው ጤና ማለት ወይም የሚዛነው የሚሰጠው ጤና አገልገሎት ደረጃ በተጠቃሚ ግለሰቦችና አጠቃላይ ሕዝቡ የሚጠብቃቸውን ተፈላጊ የጤና ልማት ግቦች ያሳካና አሰጣጡም ሆነ የሚሰጠው አገልግሉት ከጥራቱ ደረጃ ጋር ተመጣጣኝ የሙያ ክህሎት ባላቸው ባለሙያዎች ማስጠት ማቻል ነው፡፡

ጠቅለል ባለ አገላለጽ ጥራት ያለው ጤና ክብካቤ ማለት ትክክለኛ ክብካቤን በትክክለኛ ጊዜ፣ ትክክለኛውን መንገድ በማጠቀምና ለትክክለኛው ሰው ወይም ተገልጋይ በማስጠት የሚጠበቅ ትልቅ ውጤትን ማግኘት ሊባል ይችላል፡፡
ከዚህ በላይ በተሰጠው የትርጉም ማበራሪያ አኳያ ሲታይ በጤና ተቋማት የሚሰበሰብ ገቢን ለጤና ጥራት ማሻሻያነት ለማዋል በቁጥር ስድስት የሚሆኑ ዓላማዎችን ከግምት ወስጥ ማስገባት ወይም ታሳቢ ማድረግ ተገቢ እንደሆነ ይገማታል፡፡ በሌላ በኩል የጤና አገልግሎት ጥራት ማሻሻልን ግብ አድርገን በምናካሄዳቸው የሥራ እንቅስቃሴዎች አንፃር እርግጠኛ ሆነን በጥንቃቄ ማየት ያለብን ጥራትን ለማስደግ የሚከሄደው ሥራ ቢያንስ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ጥራት አሜላካች ማለኪያዎች ማካተት እንዳለበት ሚረጋገጥ ነው፡፡

***ደህንነት (safety)*** ፡- የጤና ክብካቤ በምንሰጥባቸው ወይም ለማስጠት ባሰብንባቸው ዕቃዎችና ማሪያዎች በበሽተኛውም ሆነ በጤና ባለሞያ ላይ ማንኛውም ጉዳት እንዳይደርስ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

***ውጤታማነት(effectiveness)*** ፡- የጤና የአገልግሎት አሰጣጥ በአገሪቱ የፀደቀውን የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃዎችና ፕሮቶኮሎች ብቻ ማስረት አድርጎ እንዲሰጥ በማድረግ አገልግሎት አሰጣጥን ከደረጃ በታች ወይም በላይ በማድረግ ከጥቅም ይልቅ የሚደርሰው ጉዳት የከፋ መሆኑን ተገንዝቦ ከድርጊቱ መቆጠብ ሲሆን፣ በሌላ አገላለፅ በአንድ የጤና ተቋም ወስጥ የሚሰጥ አገልግሎት ጥራት አለው ለማለል አስፈላጊ በሆኑ የአገልግሎት መስጫ ሕክምና ማሪያዎችና አቅርቦቶች ላይ ተማስርቶ አሰጣጡም በስታንዳርዱ ማስረት ሲከናወን ነው፡፡

***ታካሚ ተኮር (patient Focused)*** ፡- ጥራት ያለው ጤና ክብካቤ አገልግሎት በሚሰጥበት ሂደት ወስጥ ለታካሚው ተገቢውን ክብር ማስጠት፣ ባህላዊ እሴቱን ማጠበቅ ይገባል፣

***ጊዜን ማክበር (timeliness)*** ፡- አገልግሎት ለማግኘት የሚወሰድ ጊዜ ጥራቱን በሚዳዳድል ሁኔታ የጤና ክብካቤ ሰጪዎችም ሆነ ተቀባዩን ከሚጎዳ ማዘግየት ማጠንቀቅ ተገቢ ይሆናል፣

***የሀብት አጠቃቀም ብቃት (efficiency)*** ፡- በአነስተኛ ወጪ ከፍተኛ ጠቀሜታና ወጤት ማግኘት በሚል መርህ ላይ በመማስረት የአገልግሎት መስጫ ማሪያዎች፣ አቅርቦቶች፣ የኃይልና ማዊ ሀብቶች አጠቃቀም ላይ ብክነት እንዳይኖር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

***ፍትሐዊነት (equity)*** ፡- ፍትሀዊነት ማለት የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የተገልጋዩን የባህሪይ፣የፆታ፣የዘር ፣ የአካባቢያዊ፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ወይም በኃይማኖታዊ ልዩነት ላይ ሳይማስረት ለማንኛውም ታካሚ እኩል የጤና አገልግሎት ማስጠት ነው፡፡

***ተጠያቂነት (Accountability)*** ፡- በሕክምና አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት በሞያተኞች፣ በደንበኞች ላይ ወይም ደንበኞች በባለሞያዎች ላይ ጉዳት ቢያደርሱ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

ጥራቱን የጠበቀ የጤና አገልግሎት በጤና ተቋም ወስጥ በማገልገል ላይ የሚገኙ ከጤና ተቋሙ ኃላፊ ጀምሮ እስከታችኛው የስራ እርከን ድረስ ያሉትን ሰራተኞችን ከፍተኛ የሥራ ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት የሚጠይቅ ተግባር ነው፡፡ የጤና አገልግሎት ጥራትን ማሻሻል በቀጣይነት የሚከናወን የሥራ ሂደት እንጂ የአንድ ጊዜ ክስተት አይደለም፡፡ በመሆኑም የተቋሙን የሥራ ዕቅድና በጀት ስናዘጋጅም ሆነ የፀደቀ የሥራ ዕቅድና በጀት አፈፃፀም ትግበራ ላይ ክትትል ስናደርግ የአገልግሎት ጥራት እንደ አንድ መመዘኛ መሆኑን እርግጠኛ መሆን ይገባናል፡፡

የጠፍ አገልግሎት ጥራትን የማሻሻል ተግባር እንደማንኛውም የልማት ሥራ ወድና ብርቅ የሆነ ጊዜያችንንና ወስን የሆነ ሀብታችንን አፍሶ ማጠቀምን የሚጠይቅ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የጠፍ ጥራትን በማሻሻል ረገድ ወጪ የምናደርገው ጊዜና ወስን ሀብት ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ለማንዘብ ወይም ለማስታወስ ቀጥሎ የተጠቀሱ ምክንያቶችን ማንዘብ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

- ጥራቱን ያልጠበቀ የጠፍ አገልግሎት አሰጣጥ የራሱ የሆኑ በርካታ ጉዳቶች ያሉት ሲሆን፣ ከነዚህ ወስጥ በአገልግሎቱ ተጠቃሚ ደንበኞችን ቁጥር በመወሰን እንዲሁም ሀብትን በማባከን ገቢ እንዲቀንስ ምክንያት ይሆናል፡፡ ጥራቱን የጠበቀ የጠፍ አገልግሎት ከላይ የተጠቀሱትን ጉዳቶች እንዳይኖሩ ያደርጋል፡፡

- አንዳንድ የጠፍ አገልግሎቶችን ለማሻሻል የሚደረጉ ሥራዎች ብዙ ወጪ አይጠይቁም፡፡ ለምሳሌ አገልግሎት በማስጠት ላይ ያሉ ሠራተኞችን አማካከት ወይም የአገልግሎት አሰጣጥ አደረጃጀታችንን በማሻሻል አንፃራዊ በሆነ አነስተኛ ወጪ ያለተጨማሪ መሳሪያ ወይም የሰው ኃይል በአነስተኛ ወጪዎች የጠፍ አገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን ለማሻሻል ይቻላል፡፡
- የአገልግሎት ጥራት ለገቢ መሻሻል ምክንያት ነው፡፡ የጥራት መሻሻል ደንበኞችን በማሳብ፣የእርዳታ ሰጪዎችን ድጋፍ በማስደግ፣ዋጋን ለማሻሻል ቅደመ ሀኔታን በመፍጠር ገቢ ለማስደግ ይረዳል፡፡ ፡ ደንበኞች አብዛኛወን ጊዜ ጥራት መሻሻሉን ካረጋገጡ ለተመሳሳይ አገልግሎት ይከፍሉት ከነበረው በላይ ለመክፈል ፈቃደኛ እንደሚሆኑ ይታወቃል፡፡ ከገቢ ማደግ በተጨማሪ ጥራት ያለው የጠፍ አገልግሎት የባለሙያዎችን የሥራ ዕርካታና ተነሳሽነት በመጨመር ወጪ እንዲቀንስና ከፍተኛ ግምት ያለው ሀብት አጠቃቀም እንዲሻሻል ምክንያት ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## 2.በጤና ተቋማት ውስጥ ጥራትን ለማሻሻል የተለዩና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ተግባራት

ጥራትን የማሻሻል ተግባር በተደጋጋሚነትና ቀጣይነት ባለው መልኩ የሚተገበር የሥራ ሂደት ሲሆን እንደ ሁኔታው የእያንዳንዱን የጤና ተቋም ተጨባጭ ፍላጎት ማዕረት አድርጎ የሚፈፀም ነው፡፡ የሚከተሉት ተግባራት/ደረጃዎች በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ተከትሎ የሚፈፀም ሲሆን ከየትኛውም ደረጃ ብንጀምር የአገልግሎት ጥራቱን በማሻሻል ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ተግባራት ቅደም ተከተልና ትክክለኛነት በማየትና ገቢን ለጥራት ማሻሻያነት ለማጠቀም እንደሚረዱ ይታመናል፡፡

### *ደረጃ 1. የጥራት ማሻሻያ ዕቅድ (Planning for Quality Interventions)*

በየትኛውም የጤና ተቋም ጥራትን የማሻሻል ተግባር በሁሉም የስራ ማስኮች በአንድ ጊዜ ማምጣት አዳጋች በሆንም ጥራት የማሻሻል ዕቅድን ለጥራት ማሻሻል ቁልፍ ከሆኑ ጥቂትና ውሳኝ ሥራዎች መጀመር ይቻላል፡፡ እንደዚህ ዓይነት የሥራ ተግባራት ምርጫ ብዙውን ጊዜ ሥራዎቹ ከሚሰጣቸው የቅድሚያ ትኩረት ደረጃ፣ በሚያራቸው አንፃራዊ ማጠን ወይም በአገልግሎት አሰጣጥ ወቅት ከሚያጋጥም የችግር ተጋላጭነት አንጻር የሚወሰን ነው፡፡ ሌላው ጥራትን ለማሻሻል የሚደረግ የሥራ ዕቅድ አካል ተጠያቂ የሆነ የሰው ኃይል መመደብ ይሆናል፡፡ ይህ ጥራትን የማሻሻል ኃላፊነት የጥራት ማሻሻያ ኮሚቴ በመመሥረት ወይም በማቋቋም ጥራትን የማሻሻል ተግባር ማከናወን ይቻላል፡፡

### *ደረጃ 2. የጥራት መመዘኛ ዝርዝር ማስቀመጥ (Setting Standards and Specifictions)*

መመዘኛ(standard) ማለት ልንደርስበት ወይም ዕውን ልናደርገው ያሰብነው የጥራት ዝርዝር መግለጫ ማስቀመጥ ነው፡፡ ፡፡ በአጠቃላይ የጥራት ስታንዳርድ ዝርዝሮች የተግባር መመሪያዎች ወይም የክሊኒካል ፕሮቶኮሎች፣ አስተዳደራዊ ቅደም ተከተሎች ስታንደርድ፣ የትግበራ ቅደም ተከተል መመሪያዎች፣ የምርት ስፔስፊኬሽንስ እና የአፈፃፀም ስታንደርድ ተብለው የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እነዚህ አገር አቀፍ

የጥራት ማስጠበቂያ ስታንደርድ መመሪያዎችና ፕሮቶኮሎች ጥራትን ለማሻሻል በምንመርጣቸው ሥራዎች አካባቢ በሽታን ለመቆጣጠር እና የጤና ትምህርትን ለማስተዋወቅ የመካላከልና ተሀድሶ አገልግሎት እንቅስቃሴ በማጠቃሻነት ወይም ምንጭነት ማጠቀም አስፈላጊ ይሆናል፡፡ የትግበራና የምርት ዝርዝር መግለጫ (product specification) ሥርዓት መመሪያዎችን የሕክምና መሳሪያዎችና መድሃኒቶች አጠቃቀምና ግዥ በሚፈፀምበት ጊዜ እነዚህን መመሪያዎች ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፡፡

**መመዘኛ (standard) ሊኖራቸው የሚገቡ የአገልግሎት አይነቶች (ምሳሌ)**

- ለእናቶችና ሕፃናት ጠፍ የሚቀርቡ ማስረታዊ መድሃኒቶች አቅርቦት፣
- ተላላፊ በሽታዎችን ለመቆጣጠር የሚስያስፈልጉ የፅዳት ማስሪያዎችና አላቂ የፅዳት እቃዎች መኖር፣
- ቁልፍ የሆነ የላብራቶሪ መሳሪያዎች አቅርቦት፣
- የማቀዝቀዣ ፍሪጆች አገልግሎት ማስጠት፣
- የወሃ አቅርቦትና ስርጭት መኖር፣
- ዋናው የወሀ ስርጭት ሲቋረጥ አማራጭ የወሃ አቅርቦት መኖር፣
- የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትና ስርጭት መኖር፣
- ዋናው የኤሌክትሪክ ማስመር ሲቋረጥ አማራጭ የመብራት ኃይል አቅርቦት መኖር፣
- መደበኛ ሪኤጀንቶችና ሌሎች የምርመራ ግብዓቶች አቅርቦት መኖር፣
- የምዝገባ መዝገቦች፣ ጽህፈት መሳሪያዎችና ሌሎች የቢሮ አላቂ እቃዎች የጽዳት እቃዎች አቅርቦት መኖር፣
- በአግባቡ የተደራጀ የሪፈራል ሥርዓት መኖር/ማዘርጋት፣

## ደረጃ 3 የጥራት ማሻሻያ ተግባራት ምርጫ ለማካሄድ ችግሮችን ማየት Identifying Problems and Selecting Interventions for Improvement

የጤና ተቋም ኃላፊዎች የጤና አገልግሎት ጥራት ለማምጣት በዚህ መመሪያ በክፍል 3 ሥር ከተቀመጡ የጤና ክብካቤ ጥራት ማሻሻያ አማራጭ መንገዶች ወስጥ መምረጥ ይችላሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሥራ አስኪያጆች የጥራት ማሻሻያ ውሳኔ ላይ ከመድረሳቸው በፊት ከተቋሙ ሠራተኞች ጋር መወያየት/መጋገር፣ በአገልግሎት አሰጣጡ ሥርዓት ሂደት ላይ ትንተና ማካሄድ፣ ከታካሚ ደንበኞች የሚገኙ ግብረ መልሶች ወይም ቅሬታዎችን ማግምገም ወይም ማንኛውም ሰው ያለገደብ አስተያየቱን የሚሰጥበትን (brainstorming) መድረክ በማዘጋጀት ማስባሰብ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ እነዚህ የተዘረዘሩትን አሳታፊ የሆኑ ችግር ማየ መንገዶች ማጠቀም የተለያዩ ጠቀሜታዎችን ሊያስገኙ ይችላሉ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ችግሮችን ለማየት የምንጠቀምበት የዳሰሳ ጥናትና አጠቃላይ ወይይቶች የጤና አገልግሎቱን በተማከለ በቀጥታ በተጠቃሚነት ሆነ አገልግሎቱን በማሰጠት ባለድርሻ አካላት ያሳተፈ ስለሚሆን የጥናቱ ወጤት ከፍተኛ ተቀባይነትን ሊያገኝ ይችላል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ በተቋሙ ወስጥ ያሉ ሠራተኞች ተሳትፎ እንዲጉለብት በሚድረግ አቅማቸውን የፈቀደውን ሁሉ እንዲያበረክቱና ተባባሪ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

ለተቋማት የጥራት ማሻሻያ ሥራ የሚቋቋሙ የቴክኒክ ኮሚቴዎች ከዚህ በላይ በተጠቀሰትና ሌሎች መንገዶችንም በማጠቀም የተለያዩ የጥራት ችግሮችን የማየት ሥራ ካጠናቀቁ በኋላ ቀጣዩ ተግባር የሚሆነው መመዘኛዎችን በማዘጋጀት በጥራት ማሻሻል ተግባር ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባቸውን ችግሮችን ይለያሉ፡፡ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ተግባራት የሚዘጋጁ መመዘኛዎች የግለሰብን ሳይሆን የቡድኑን ትኩረት አቅጣጫ ማንፀባረቅ ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህ መመዘኛዎች የሚወሰነውን ወሳኔ ግልፅና አሳማኝና የተሟላ እንዲሆን አጋዥ ሊሆኑ ይገባል፡፡ መመዘኛ ነጥቦች በዋናነት ሊያካትቱት ከሚገቡ ጉዳዩች ወስጥ ጥራትን ለማሻሻል የተመረጡ ተግባሮች በቴክኒክ በኩል ለተፈፃሚነት ያላቸው አዋጭነት፣ የሕዝቡን የጤና ደረጃ ለማሻሻል የሚኖራቸው ተጽዕኖ እና ለመተግበር በቂ የሆነ ሀብት ሊገኝላቸው መቻሉ ሊጠቀሱ የሚገባቸው ናቸው፡፡ ኮሚቴው ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ጥራት ማሻሻያ ችግሮችን ለመምረጥ የተለያዩ የቡድን ውሳኔ አሰጣጥ መንገዶች ለምሳሌ እንደ ቅደም ተከተል ማስቀመጥ፣ድምፅ የማሰጠት አሰራር ወይም ዲሲሽን ማትሪክስ ማጠቀም ይቻላል፡፡

## ደረጃ 4 ችግሮችን መግለጽ (Defining the Problem)

የጥራት ማሻሻያው ቡድን ችግሮችን ከለየ በኃላ በነዚህ ችግሮችና በጤና ጥራት ዙሪያ በተዘጋጁ መመሪያዎችና ስታንዳርዶች መካከል ያለውን ልዩነት ያብራራል፡፡ ችግሩን ለማወቅ የሚቀርበው ማብራሪያ በተጨባጭ ያሉ ችግሮችንና ችግሮቹ እንዴት ተፅዕኖ እያሳዳሩ እንደሆነ የሚያሳይ መረጃ ሊያቀርብ ይገባል፡፡ ግልፅ በሆነ መንገድ የችግሮቹ መነሻና መድረሻ የት እንደሆነ እና እንዲሁም እነዚህ ችግሮች ቢቀረፉ ሊመጣ የሚችለውን ለውጥ ማወቅ አለበት፡፡

የችግሮች ምንነት መግለጫ ለማዘጋጀት ጥራትን ለማሻሻል በሚደረግ የሥራ ሂደት ደረጃዎች ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ወሳኝ ተግባር ነው፡፡ የችግሮች ምንነት መግለጫ ማዘጋጀት በጣም አስፈላጊ ሲሆን የማለየቱን ስራ አቅልለን ማየት አይገባም፡፡ብዙዉን ጊዜ የችግሮች የመጀመሪያ አቀራረብ የችግሮችን ምክንያት ብቻ ለይቶ የማቅረብ ሁኔታ ይታይበታል፡፡ ለምሳሌ 'ላብራቶሪ የለንም' ለሚለው ችግር ተጨማሪ 'የሰው ኃይል ያስፈልገናል' ብሎ መፍትሄ ማስጠት የተሟላ ሊሆን አይችልም፡አንዳንድ ጊዜ ችግሮችን ጠቅለል ባለ ሚልኩ ማቅረብ መፍትሄ ለማስጠት ያስቸግራል--- ለምሳሌ 'በቡድን ማስራት አንችልም'. የችግሮች መግለጫ ችግሩን ከማብራራት ይልቅ ሌላዉን ጥፋተኛ አድርጎ ሊቀርብ ይችላል፡፡ ለምሳሌ 'ነርሶች ታካሚዎችን በትህትና አያስተናግዱም'. በሚለት ቢቀርብ ችግሩን ለመፍታት የሚያስችል ተጨባጭ የሆነ መፍትሄ ለማስጠት አያስችልም፡፡ በመሆኑም የችግሮች መግለጫ ሲዘጋጅ በሚያሻማ መንገድና ከአገልግሎት ጥራት ችግሮች ወይም ከህብረተሰቡ የጤና ሁኔታ ጋር የተቆራኘ ሆኖ መቅረብ አለበት፡፡ በሌላ አገላለፅ የችግሮች መግለጫ አንድን ተለይቶ የሚታወቅ የሥራ ሂደት ወይም ሥራ እንቅስቃሴ የግድ ማስረት አድርጎ የሚዘጋጅ ከሆነ ጥራትን ለማሻሻል የሚደረገዉን ጥረት በትኩረት ለማካታተልና አፈፃፀማንም ለማካካት ይቻላል ወይም ቀላል ይሆናል፡፡ ቀጥሎ እንደ ምሳሌ በቀረበው ሰንጠረዥ ላይ የችግሮች መግለጫ አዘገጃጀት ተሜልክቷል፡፡

| ተ.ቁ | ደካማ የችግሮች መግለጫ | በችግሩ አቀራረብ ላይ የሚስተዋል ደክመት | የተሻሻለው የችግር መግለጫ አቀራረብ |
|---|---|---|---|
| 1 | ጥራት ያለው የላብራቶሪ መሳሪያ የለንም | የችግሩ አቀራረብ የችግሩን ምክንያት ብቻ በማያዝ የተዘጋጀ ነው | ምንም እንኳን የሳንባ ነቀርሳ በሽታ እንዳለባቸው የተጠረጠሩ ቢኖሩም ባሁኑ ጊዜ የላቦራቶሪ አገልግሎቱን ማግኘት የቻሉት 25% ብቻ ናቸው |
| 2 | ተጨማሪ የሰው ኃይል ያስፈልጋል | መግለጫው የያዘው ሜልስ ያልተሟላና ጥቅል ነው | በጤና ጣቢያ ለማልገል ከሚማጡ በሽተኞች 30% የሚሆኑ በሽተኞች ያለ አገልግሎት እንዲመለሱ ይደረጋል |

***ደረጃ 5 <u>የችግሮችን ማሻ ምክንያት ከምንጩለማየት የሚደረግ ትንተና</u>***

ትርጉም ያለወና ዘለቄታዊ የሆነ ጥራት ማሻሻል ተግባር በቅድሚያ ለጥራት አለማሻሻል ምክንያት የሆኑ ችግሮችንና የእነዚህን ችግሮች መንስኤ በሚገባ ለይቶ በማወቅ ላይ የሚማስረት ነው፡፡ በተለይ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ተግባር ወስብስብ እንደመሆኑ የችግሮችን ሥርና መንስኤ

በግልፅ ለማወቅ አግባብ ባላቸው የጥናት ዘደዎች ላይ ተመሥርቶ ጠለቅ ያለ ትንተና ማድረግን የሚጠይቅ ይሆናል፡፡ የችግሮችን ሥርና ማስኤ ለማወቅ ከምንጠቀምባቸው ስልታዊ የትንተና መሳሪያዎች ወይም መንገዶች ወስጥ ለምን-ለምን መካራ (Why-Why Exercises) ፣ ፍለው ቻርት፣ የምክንያትና ወጠት(cause and effect) ዳያግራም የሚባሉት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እነዚህን የተለዩ ዘደዎች በማጠቀም በርካታ የችግር ማስኤዎች ከተለዩ በኋላ የጥናት ቡድኑ ከነዚህ ወስጥ የትኞቹ ችግሮች ከፍተኛ ተፅዕኖ ሊያደርሱ እንደሚችሉ ማየት ይኖርበታል፡፡ በዚህም ከአጠቃላይ ማስኤዎች ከሁለት እስከ ሶስት የሚሆኑ ምክንያቶች ለአብዛኛው የጥራት ችግር ማስኄ ሆነው ሊሚጡ ይችላሉ፡፡

## ክፍል ሦስት

## 3.የወስጥ ገቢን ተጠቅሞ ጥራትን ለማሻሻል ቅደሚያ የሚሰጣቸው ተግባራት

የኢትዮጲያ መንግሥት በሁሉም የአስተዳደር ዕርከን ባሉ የመንግሥት አካላት የሚደረገው የበጀት ፍሰት የተጠቃለለ የበጀት ሥርዓትን የተከተለ ነው፡፡ በተጠቃለለ የበጀት አሰራር ሥርዓት ማንኛወም የመንግሥት ግምጃ ቤት በጀት በተጠቃለለ ቋት ወስጥ እንዲገባ ከተደረገ በኋላ ሁሉም የመንግሥት ተቋማት ለሚያካሄዱት ዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴ ደመወዝና ሥራ ማስኬጃ ከተጠቃለለው ፈንድ በዓመታዊ የበጀት ዕቅዳቸው ማስረት የፋይናንስ ፍሰት ይደረግላቸዋል፡፡ በተመሳሳይ ሜኩ እንደሌሎች የመንግሥት ተቋማት ጤና ተቋማትም አገልግሎት በማስጠት ይሰበስቡት የነበረው ገቢም ወደዚሁ ወደ ተጠቃለለው የመንግሥት ግምጃ ቤት ፈሰስ ይደረግ ነበር፡ ከጤና ተቋማቱ ተሰብስቦ ወደ መንግሥት ግ/ቤት ፈሰስ ይደረግ የነበረው ገንዘብ በማጠን አነስተኛ የነበረ ሲሆን፣ አነስተኛ እንዲሆን ካደረጉት ምክንያቶች ወስጥ የነጻ ህክምና ሥርዓት አለመኖር በተቋማቱ ወስጥ ያሉ ሠራተኞች የባለቤትነት ስሜት አነስተኛ መሆንና የአቅም ወስንነትም ጭምር እንደሆነ ይታመናል፡፡

በሌላ በኩል እነዚህ የጤና ተቋማት ብዙ ጊዜ በነበረባቸው ከፍተኛ የበጀት እጥረት ለተለያዩ ስራዎች የሚያስፈልጋቸወን ወጪዎች ለማሸፈንና ማስረታዊ የሆኑና ለጤና አገልግሎት ሥራ ግብአት የሆኑ መድሃኒቶችንና የላብራቶሪ ምርመራ አቅርቦቶችን ለማሟላት አይችሉም ነበር፡፡ በነበረው የበጀት እጥረት ምክንያት በጤና ተቋማት ወስጥ ማስረታዊ መድሃኒቶችና ሌሎች ለምርመራ አስፈላጊ የሆኑ ቋሚ አላቂ

ግብአቶች ተሟልቶ አለመገኘት በአገሪቱ በሚገኙ ጤና ተቋማት ውስጥ ያለው የጤና አገልግሎት ጥራት ደካማ ሆኖ እንዲገኝ ምክንያት ሆኗል፡፡

በአራተኛው የናሽኛል ሄልዝ አካወንትስ /በ2002 ዓ.ም(National Health Accounts) ግምት መሰረት የአንድ ሰው አማካይ ዓመታዊ የጤና ወጪ 16 የአሜሪካን ዶላር ወይም 217 ብር ብቻ ሲሆን፣ ይህም የዓለም አቀፍ ጤና ድርጅት ለዝቅተኛ መሰረታዊ ጤና አገልግሎቶች ወጪ እንዲሆን ካስቀመጠው ዝቅተኛ የወጪ መጠን 34 የአሜሪካን ዶላር ወይም 464 ብር የ47 በመቶውን ድርሻ ብቻ ይይዛል፡፡ የኢትዮጲያ ዓመታዊ አማካይ የነፍስ ወከፍ ወጪ ደህነት በነገሰበት ከሳብሰሃራ አገሮች አማካይ 163 ብር ጋር ሲነፃፀር በጣሙ የተሻለ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡
ለጤና ተቋማት የሚመደብ በጀት በቂ ላለመሆኑ አብዛኛውን ጊዜ የመሰረታዊ መድሃኒት ክምችታቸው እና ለተለያዩ ምርመራዎች የሚጠቀሙባቸው ሪኤጀንቶች እጥረት መታየት በተደረጉ ጥናቶች ላይ በዋና ማስረጃነት የታየ ነው፡ ይህንንም ችግር በማንዘብ የኢትዮጲያ ፌዴራላዊ መንግሥት የጤና ክብካቤና ገንዘብ ማግኛ ስልትን በ1991ዓ.ም አፅድቋል፡፡

በዚህ ስልት ውስጥ ከተካተቱ የገንዘብ ማግኛ አማራጭ መንገዶች አንዱና ዋናው የጤና ተቋማት አገልግሎት በመስጠት የሚሰበስቡት ገቢ ከመንግሥት ግምጃ ቤት በጥቅል ከሚመደብላቸው በጀት በተጨማሪነት እንዲጠቀሙበት የተፈቀደው ነው፡ ይህንን ስልት ተግባራዊ ለማድረግ የጤና ሴክተር ክብካቤና ገንዘብ ግኝት ማሻሻያ ፕሮግራም ተነድፎ በተግባር እንዲውልና ገቢው ለጥራት ማሻሻያ መዋል እንዳለበት በግልፅ የሚያሳይ የሕግ ማዕቀፍ/አዋጅ፣ደንብና መመሪያ/ ተዘጋጅቶና ፀድቆ በስራ ላይ እየዋለ ነው፡

በጤና ሴክተር ልማት ሰነድም ሆነ በሚኒየም የጤና ልማት ግቦች ላይ እንደተጠቀሰው ጤና ተቋማት ከሚሰጡት አገልግሎት የሚሰበሰቡትን ገቢ በራሳቸው እንዲያወሉት የሚጠበቀው የጤና አገልግሎት ጥራትን በሚያሻሽሉ ወጪዎች ላይ ነው፡ በመሆኑም ከውስጥ የሚገኝ ገቢ አጠቃቀም ከዚህ በመቀጠል ለአገልግሎት ጥራት ማሻሻል ባላቸው ፋይዳ ተለይተው በተገለጹት የሥራ ዝርዝሮች ቅደም ተከተል መሰረት ይሆናል፡፡

**በመጀመሪያ ደረጃ ትኩረት የሚሰጣቸው ተግባራት፣**

- የፋርማሲ አገልግሎት/ዝርዝሩ በዕዝል 1 ላይ ታይቷል/፣
- የሕክምና መሳሪያዎችና አቅርቦቶች /ተራ ቁጥር 5.1 እና ዕዝል 1 ላይ ታይቷል/፣
- ከህክምና አገልግሎት ጋር ቀጥታ ተያያዥነት ያላቸው የመሰረተ ልማት ግንባታ ዝርዝሩን ተራ ቁጥር 5.7 ላይ ይመለከቱ/፣
- ለንፅህና አገልግሎቶች ማሻሻያ/ዝርዝሩ ተራ ቁጥር 5.8 ላይ ተመልክቷል/፣
- ለበሽታ መከላከልና የጤና ማጎልበት ትምህርታዊ አገልግሎቶችን ለማጠናከር /5.9 ላይ ይመልከቱ/፣

- የቅብብሎሽ ሥርዓትን ለማሻሻል /5.13 ላይ ይመልከቱ/፣
- ለበሽታዎች ቁጥጥር ሥራ /ዝርዝሩን በሀገር አቀፍ የበሽታዎች ቁጥጥር መመሪያ ላይ ማየት ይቻላል/፣
- ለተቋሙ የቦርድ/ ከፍተኛ አመራር አባላት የሚከፈል ክፍያ፣

**በሁለተኛ ደረጃ ትኩረት የሚሰጣቸው ተግባራት፣**

- የተቋሙ መረጃ ሥርዓት ለማሻሻል/ዝርዝሩ በ5.11 ተመልክቷል/፣
- የአገልግሎት መስጫ ክፍሎችን ለማስፋፋት፣
- ለስልጠናና ለተለያዩ ጥናቶችና ምርምሮች/5.10 ይመልከቱ/፣
- ለድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶች ግንባታና ጥገና፣
- ሕክምና ነክ አገልግሎቶችን ለሶስተኛ ወገን ለመስጠት ተግባር፣
- የሂሣብ አስተዳደር ሥርዓትን ለማሻሻል፣

**በ3ኛ ደረጃ ትኩረት የሚሰጣቸው ተግባራት፣**

- የቢሮ ቋሚ ዕቃዎች፣
- በሁለተኛ ትኩረት ውስጥ ያልተካተቱ ሌሎች ሥልጠናዎች፣
- የቢሮ ውስጥ ቋሚ መሣሪያዎች፣
- ለተለያየ ሥራ ማስኬጃዎች ወጪ
- ለተቋሙ ሠራተኞች ማበረታቻ፣

**<u>የጤና ተቋማት በውስጥ ገቢያቸው የሚጠቀሙባቸው/የሚፈቀዱ/ ዝርዝሮች</u>**

ከዚህ በላይ የውስጥ ገቢን ለመጠቀም እንዲቻል ቅደምተከተል እንደተቀመጠ ሁሉ በውስጥ ገቢ ለመጠቀም የማይፈቀዱ ተግባራትንም ማስቀመጥ ተገቢ ይሆናል፡፡ ቀጥሎ የተጠቀሱት ዝርዝሮች የጤና ተቋማት በውስጥ ገቢያቸው መጠቀም የሌለባቸው ወጪዎች ናቸው፡፡

ሀ. ማንኛውም የውጭ አገር ጉዞና ሥልጠና፣

ለ. ከ3 ወር በላይ ለሆነ ጊዜ የሚሰጥ የአገር ውስጥ ሥልጠና፣

ሐ. ማንኛውም ከህክምና አገልግሎት ውጭ ያሉ በገንዘብም ሆነ በዓይነት ለሶስተኛ ወገን የሚሰጥ ስጦታ፣

መ. ለአማካሪዎች ቅጥር ወይም ክፍያ፣

ሠ. የውስጥ ገቢ ጥቅም ላይ እንዲውል ከተጠቀሱ የግንባታ ዓይነቶች ወጪ

ረ. የውስጥ ገቢን በመጠቀም ረገድ ከተዘረዘሩ ዓላማዎች ማስፈፀሚያ ወጪ

ሰ. የጤና ጣቢያው ከፍተኛ አመራር ወይም የሆስፒታሉ ቦርድ ከፈቀደው የወጪ አርዕስት ወይም ሥራ ወጪ የውስጥ ገቢን ማጠቆም አይቻልም፡፡ ከዚህ በላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ቀጥሎ የማቀርበው ደግሞ የጥራት ማሻሻል ሥራ በሚከሄደበት ሂደት ውስጥ ያሉ ቁልፍ ጉዳዮችና

የቅድሚያ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ምን እንደሆነ እንዲሁም ተግባራቱ በሚከናወኑበት ወቅት የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ አሠራር እንዴት ሚካናወን እንዳለበት ነው፡፡

## ክፍል አራት

## 4.የጥራት ማሻሻያ ተግባር ዕቅድና አፈጻጸም

በማንኛውም የጤና ተቋም ወስጥ ያለንን ሀብት የጤና ተቋማን አገልግሎቶች ለማሟላት በምናቅደበት ጊዜ ዋነኛ መመዘኛ መሆን የሚገባው ጉዳይ ወጪ ሊጠየቅባቸው የታቀዱት አገልግሎቶች በጤና ተቋሙ ወስጥ ያለወን ጥራት ለማሻሻል አስተዋፆ ያደርጋሉ ወይንስ አያደርጉም የሚለው ነው፡፡ በዚህ ረገድ የጤና ተቋማት ይህንን ለጤና ተቋሙ አገልግሎት የሚውል ሀብት በሚጠቀሙበት ጊዜ ተቋማዊ በሆነ ሚልኩ የአሠራር ሥርዓት በማውጣት የመደበኛው ዕቅድ ዝግጅትና አፈጻጸም የሥራ ሂደት አካል ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

የጤና ተቋማት የወስጥ ገቢያቸወን ተጠቅመው የሚያካሂዱት የጥራት ማሻሻያ ተግባር ምርጫም ሆነ የዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዢ ሚኑ በሚኑ የመንግሥትን የዕቃና አገልግሎቶች ግዢ ደንብና መመሪያ ተከትሎ የሚፈፀም ሲሆን፣ ከነዚህ ወስጥ ቀጥሎ የተጠቀሱት በዋናነት ሊከተሉት የሚገባ አሠራር ሂደት ነው፡፡

## I. ጥራትን ለማሻሻል የሚገዙ ዕቃዎችንና የሚሻሻሉ አገልግሎቶችን የሚመርጡ የባለሙያዎች ቡድን ማቋቋም፣

የቡድኑም ስብጥር ከጤና ተቋሙ የተለያዩ የሥራ ክፍሎች፣ ተወካዮችን ማለትም የተቋሙን ኃላፊ፣ ከፋይናንስና ከግዢ አፊሰር ወዘተ..... የተውጣጡ ሰዎችን በማካተት ሊቋቋም ይችላል፡፡

የዕቃዎችና አገልግሎቶች ምርጫና ግዢ ኮሚቴ ሊያከናወናቸው ከሚገቡ ተግባርና ኃላፊነቶች ወስጥ ዋናዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡

ሀ. ለጥራት ማሻሻያ ወሳኝ የሆኑና ነገር ግን በመደበኛው የመንግሥት ግዢ ሊሟሉ ያልቻሉ ዕቃዎችንና አገልግሎት ዓይነቶችን ይለያል፡፡ ይህንን አስፈላጊ የሆኑ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማለየት ሥራ ሲያከናወን የዕቃዎችን በተቋሙ ወስጥ አስፈላጊነትና ስታንዳርድ ለማወቅ ከሚጠቀምባቸው መንገዶች ወስጥ የተለያዩ የሥራ ክፍሎችን ተዘዋወሮ መመልከት ወይም መቃኘት፣ ከድጋፍ ሰጪ የቴክኒክ ሠራተኞች ጋርና ሜጅመንት ቃለ-መጠይቆችንና ወይይቶችን በማካሄድ እንዲሁም የተለያዩ ቋሚ ዕቃዎችንና አቅርቦቶችን ስታንደርድ ማዘፀር የሚጠቀሱ ናቸው፣

ለ. የተለያዩ አሠራር መንገዶችን በማጠቀም የጥራት ችግር ከፍተትን ለመሙላት

አስፈላጊ ናቸው ተብሎ የተለዩ ዕቃዎችንና አገልግሎቶች ዝርዝር በወስጥ ገቢ ለማጠቀም ከተፈቀዱና ካልተፈቀዱ ዝርዝሮች ጋር በማነፃፀር ግምገማ ሚድረግና በመቀጠልም ቀዳሚ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ተግባራትን ይለያል፡፡

ሐ. ቅድሚያ ሊተገበሩ ይገባል የተባሉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማሟላት ተግባራትን መሰረት በሚድረግ የወጪ ግምት ማዘጋጀት፣ የወጪ ግምት ሲዘጋጅ የሚወጣው ገንዘብ ጣሪያ ታሳቢ የሚያደርገው በባንክ የተጠራቀመና በበጀት ዓመቱ ከተለያዩ ምንጮች ይሰበሰባል ተብሎ የተገመተ ገቢ ድምርን ይሆናል፡፡

ከወስጥ ገቢሊገዙ የታቀዱ እቃዎችና አገልግሎቶችን በተግባር ላይ ለማዋል የድርጊት መርሀ ግብር ያዘጋጃል፡፡፡

መ. ይህንን የተዘጋጀውን ዕቅድና የማስፈፀሚያ የጊዜ ሰሌዳ በተቋሙ ጥራት ማሻሻል ላይ የሚሰራው በጎ ተፅዕኖ ለይቶ በሚወቅ ከሚያስችል መግለጫ ጋር ለጠና ተቋማት ቦርድ ወይም ከፍተኛ አመራር ይቀርባል፡፡

<u>**ማስታወሻ**</u>፡ – የጥራት ማሻሻያ ቡድኑ ከዚህ በላይ በተዘረዘረው ተግባርና ኃላፊነት መሰረት የሚያከናውነው ጥናታዊ የዳሰሳ ሥራና በመጨረሻም የደረሰበት የውሣኔ ሀሳብ የሚያሳይ ሰነድ ሰርቶ ለማጠናቀቅ እጅግ ቢበዛ በሁለት ወር ጊዜ (ጥርና የካቲት) ማጠናቀቅ ይኖርበታል፡፡ ይህንን የጥናት ወጤት በአግባቡ ለመገምገም፣ ለመደገፍና በጠና ተቋሙ ዓመታዊ የስራ ዕቅድ ወስጥ ለማካተት በቂ ጊዜ ነው፡፡

## II. <u>የቀረበውን ጥራት መገምገሚ በጠና ተቋሙ ኃላፊ ማፀደቅ</u>

በዚህ የሥራ ሂደት ሥር የሚከተሉት ተግባራት ይከናወናል፡ –

- በአጥኚ ኮሚቴ ተዘጋጅቶ የቀረበው ጥናትና የውሣኔ ሀሳብ በጠና ተቋሙ የሜጅመንት ኮሚቴ ይገመገማል፣
- የጠና ተቋሙ ሜጅመንት ኮሚቴ ግምገማውን በሚያካሄድበት ወቅት በትኩረት ታሳቢ አድርጎ ከሚመለከታቸው ጉዳዮች ወስጥ የተከናወነው ጥናት ለጥናቱ ሥራ የተዘጋጁ የአሰራር ሥርዓቶችንና ደረጃዎችን ጠብቀው የተከናወኑ መሆኑን፣ በእንያንዳንዱ የሥራ ክፍል የሚታዩ የጥራት ክፍተቶችን በትክክል ለይቶ ያሳየ መሆኑን፣ በጥናቱ ወስጥ የተካተቱ ተግባራት ከወስጥ ገቢ አጠቃቀም መመሪያዎች ጋር የተጣጣመ መሆኑን፣ እንዲሁም በጥናቱ ዙሪያ የቀረበውን የውሣኔ ሀሳብ ጥራትን ለማሻሻል ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ተግባሮች እንዲሁም ከዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዢ ቅድሚያ ትኩረት ጋር የተገናዘበ መሆኑን በቂ መግለጫ የቀረበበት መሆኑን ማየት የሚጠቀሱ ናቸው፣

- በተጨማሪም የጠፍ ተቋሙ ሜጅመት ኮሚቴ በጥናት ቡድኑ ቅድሚያ ትኩረት እንዲያገኙ የተሚጡ ሥራዎች ጥራትን ለማሻሻል ያላቸዉን ጠቀሜታና ተቋሙ በወቅቱ በባንክ ያለዉን ይሰበሰባል ብሎ በሚያስበው የገንዘብ አቅም ሊፈፀሙ መቻል አለመቻላቸዉን ለማወቅ ንፅፅራዊ ግምገማ ያካሄዳል፣

ከላይ በተጠቀሱ መንገዶች በተቋሙ ሜጅመንት ኮሚቴ ተገምግሞ በቀረበው ጥናት ላይ የተደረጉ ለውጦችም ካሉ ተካተው የዘመኑ ወቅታዊ የሥራ ዕቅድ አካል ሆኖ እንዲፀድቅ ለጠፍ ተቋሙ ከፍተኛ አመራር ወይም ቦርድ ይቀርባል፡፡

## III. በጠፍ ተቋሙ አመራር አካል ማፅደቅ

መጀመሪያ በአጥኝ ቡድን ተዘጋጅቶና በተቋሙ የሜጅመንት ኮሚቴ ተገምግሞ ለተቋሙ ከፍተኛ አመራር/ቦርድ ቀርቦ እንዲፀድቅ ይደረጋል፡፡ የተቋሙ አመራር አካላት የቀረበላቸዉን የውስጥ ገቢ አጠቃቀም ዕቅድ ለማፅደቅ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናሉ፣

- በውስጥ ገቢ እንዲተገበር በተቋሙ ሜጅመንት የቀረበው የሥራ ዕቅድ ተቋሙ ከመንግሥት ግምጃ ቤት በጥቅል በሚያገኘው የድጋፍ በጀት የሚሰሩ ተግባራት ወስጥ ባለማካተት የተዘጋጀ መሆኑን ይገመግማል፡
- ማንኛውም አስፈላጊ የሆኑ ለውጦችንና ማስተካከያዎች ካደረገ በኋላ የዘመኑ ዕቅድ ሆኖ ተግባራዊ እንዲሆን የሚጸድቅ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## IV. የውስጥ ገቢን ለማጠቀም ማስወጅ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በወጣው የጠፍ አገልግሎት አሰጣጥ የጠፍ ተቋምት አስተዳደርና አመራር ደንብ ወይም መመሪያ እንዳስቀመጠው ከጠፍ ተቋማት የሚሰበሰብ ገቢ ለማጠቀም በቅድሚያ በየደረጃው ባሉ ተቋማትዓመታዊ በጀት ወስጥ በማካተት ቀርቦ ማታወጅ ይኖርበታል፡፡

## V. የውስጥ ገቢ ዕቅድ አተገባበር

- የጠፍ ተቋሙ ሜጅመንት ኮሚቴ የጥራት ማሻሻያ ሥራም ሆነ የዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዢ በፀደቀው ዕቅድ ማስረት ማከናወኑን ማከታተል ይኖርበታል፣
- የጠፍ ተቋሙ ሜጅመንት ኮሚቴና የተቋሙ ቦርድ/ከፍተኛ አመራር የተቋሙ የግዢ አፈፃፀም በዕቅዱ ማስረት ማከናወኑን ብቻ ሳይሆን የሚከሄደው የዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዢ ሙሉ በሙሉ የመንግሥት አሰራር ሂደትና መመሪያዎችን ተከትሎ እየተፈጸመ ስለመሆኑ ጥብቅ ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

## የመንግሥት ዕቃና አገልግሎት ግዢ የሥራ ሂደት ደረጃዎች

*ለህክምና አገልግሎቶች የጥራት ማሻሻያ ኮሜቴ/ቡድን ማቋቋም*

↓

*በተቋሙ ሜጅመንት ኮሜቴ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ተግባራትና የግዢ ዓይነቶችን ገምግሞ የሚገፍ ሥራ*

↓

*በተቋሙ የአሜራር አካላት/ቦርድ/ዕቅዱን ሜደቅ*

↓

*በአሜራር አካል የፀደቀወን የሥራና የግዢ ዕቅድ በዓመታዊ የተቋሙ ዕቅድ ወስጥ እንዲካተት ይደረጋል*

↓

*በሚሟከተው አካል የፀደቀወን ዓመታዊ ዕቅድ ማተግበር*

## ክፍል አምስት

## 5. የወስጥ ገቢን ለማጠቀም የተፈቀዱ የሥራ ዝርዝሮች

በጤና ሴክተር ልማት ፕሮግራም ሰነድ ላይ እንደተገለፀው አንዱና ዋንኛው ሊደረስበት የሚገባ የልማት ግብ የጤና ተደራሽነትንና የአገልግሎት አሰጣጥ ጥረትን ለማሻሻል እገዛ የሚያደርጉ አስፈላጊ የሆኑ የሕክምናና የቢሮ ቋሚ ዕቃዎችና አቅርቦቶችን ማሻሻል ነው፡፡ የቋሚ የሕክምና ዕቃዎችና አቅርቦቶች በበቂ ሁኔታ ማግኘት በበኩሉ በጤና ተቋሙ ወስጥ የሚሰጥ የጤና ክብካቤ አገልግሎት እንዲሻሻል ያደርጋል፡፡ በመሆኑም የጤና ተቋማት ቢያንስ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ባወጣው የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድን በተከተለ ሜልኩ በአስፈላጊ የሕክምና ዕቃዎችና መሳሪያዎች እንዲሁም በሌሎች የአገልግሎት ጥራትን ለማሻሻል ዕገዛ በሚያደርጉ መሳሪያዎች ተደራጅተው ሊቆዩ ይገባል፡፡ በመሆኑም የጤና ተቋማት ከመንግሥት ግምጃ ቤት እና ከተለያዩ ዕርዳታና ብድር ምንጮች ከሚያገኙት የፋይናንስ ድጋፍ በተጨማሪ

አገልግሎት በሚሰጡት የሚሰበሰቡትን ገቢ ለአገልግሎት ማሻሻያነት እንዲወሉ ተፈቅዶላቸዋል፡፡ ከዚህ በመቀጠል የጤና ተቋማት በወስጥ ገቢያቸው እንዲጠቀሙ የተፈቀዱ የተለያዩ የጥራት ማሻሻያ ዝርዝሮች የቀረበበት ነው፡፡

## 5.1 <u>የሕክምና ዕቃዎች ዝርዝር</u>

<u>በጤና ጣቢያዎች ደረጃ</u>

የጤና ተቋማት የወስጥ ገቢ በጤና ጣቢያዎች ደረጃ የሚከተሉትን የሕክምና ዕቃዎች ለመግዛት ወይም ለማጠገን ሊወል ይችላል፡፡ ዝርዝሩን በዕዝል ላይ መመልከት ይቻላል፣

1. የሕክምና መመርመሪያ ዕቃዎች፣
2. የማዋለጃ ዕቃዎችና መሣሪያዎች፣
3. የቀዶ ጥገና  አገልግሎት መሣሪያዎች
4. ከህዋስ ነጻ ማድረጊያ መሳሪያዎች (እቃዎች) Sterilization፣
5. የመመርመሪያ መሳሪያዎች፣
6. የላብራቶሪና ለምርመራ ማዘጋጃ መሳሪያዎች፣
7. የእናቶችና ሕፃናት ሕክምና መሳሪያዎች፣
8.  ለሕክምና የሚያገለግሉ መሳሪያዎች፣
9. የመድሃኒት ክፍል መሳሪያዎች፣
10. ተኝተው ለሚታከሙ ለአዋቂ ወንዶችና ሴቶች ሕክምና ክፍል የሚያገለግሉ መሣሪያዎች፣
11. ለበሽታ መከላከል የሚያገለግሉ መሳሪያዎች፣
12. ሌሎች ማንኛወም በጤና ጥበቃ ሚኒሰቴር ለሕክምና አስፈላጊ ናቸው የሚባሉ የሕክምና መሳሪያዎች፣

<u>**ለሆስፒታሎች አገልግሎት የሚውሉ**</u>

ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት መሳሪያዎች ደግሞ በሆስፒታል ደረጃ ለሚደረግ የጤና ጥራት ማሻሻያ ሥራ ሊሟሉ ከሚገቡ ዝርዝሮች ወስጥ የሚመደቡ ናቸው፡፡

1. የወስጥ አካል መመልከቻ መሳሪያዎች፣
2. የላብራቶሪ ዕቃዎች፣
3. የማሕፀንና ፅንስ ሕክምና መሳሪያዎች፣
4. ለቀዶ ጥገና የሚያገለግሉ መሳሪያዎች፣
5. የተዋህሲያን መግደያ/ (Sterilization/ Autoclave፣
6. ለተመላላሽ ሕክምና ለጥርስና ዓይን ሕክምና፣
7. የእናቶችና ሕፃናት ሕክምና መሳሪያዎች፣
8. የመድሃኒት ቤት ዕቃዎች፣

9. ተኝተው ለሚታከሙ የአዋቂ ወንዶችና ሴቶች ሕክምና ክፍል የሚያገለግሉ መሣሪያዎች፣

10. ተኝተው ለሚታከሙ የሕፃናትና ገና ለተወለዱ ሕፃናት ሕክምና ክፍል የሚያገለግሉ መሣሪያዎች፣

11. ለብቻቸው ተለይተው ሕክምና ለሚደረግላቸው ሕሙማተኞች የሚያገለግሉ Isolation room፣

12. በነርሶች ክፍል የሚገኙ ለሕሙማን አገልግሎት የሚሰጡ መሣሪያዎች Nurse station፣

13. የአስከሬን ምርመራ መሳሪያዎች፣

14. ለድንገተኛ ሕክምና ክፍሎች የሚያገለግሉ መሣሪያዎች፣

15. ለጽኑ ህሙማን የሚያገለግሉ መሣሪያዎች፣

16. የፊዚዮቴራፒ ዕቃዎች፣

17. ማንኛውንም በጤና ጥበቃ ማስፈርት ማሰረት ለሕክምና አስፈላጊ የሆኑ ዕቃዎች፣

## 5.2 የሕክምና አቅርቦቶች

ሀ. በጤና ጣቢያዎች ደረጃ

በጤና ጣቢያዎች ደረጃ ለአስተኝቶ ማከም የሚያገለግሉ አቅርቦቶች ዝርዝር በአዝል---ይመልከቱ፡፡ በቀጣይ በሚከለሰው ሀገራዊ እስታንዳርድ መሠረት የሚታይ ይሆናል፡፡

የጤና ጣቢያዎችን ጥራት ለማሻሻል የጤና ተቋሞች የወስጥ ገቢ ቀጥሎ የተጠቀሱትን ማለትም -

- መሠረታዊ መድኃኒቶችንና ሌሎች ማንኛወም አስፈላጊ ግብአቶችን
- ለምርመራ ስራ የሚውሉ የተለያዩ ኬሚካሎችና ሌሎች ማንኛውም በማስፈርቱ የተካተቱ አስፈላጊ ግብአቶች ማሟያ ይወላል፡፡

ለ. በሆስፒታል ደረጃ

በሆስፒታል ደረጃ የወስጥ ገቢ ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩ የሕክምና ነክ አቅርቦቶች ማሟያ ሊወል ይችላል፣

1. የወስጥ አካላትን ለመመልከት ለተገዙ የሕክምና ዕቃዎችና መሳሪያዎች አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎች፣
2. የምርመራና ሌሎች ተፈላጊ ኬሚካሎች ግዡ
3. ለፊዚዮቴራፒ አገልግሎት የሚውሉ፣
4. ለመሠረታዊ መድኃኒቶች፣

5. ሌሎች ማንኛወም አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶች ማሟያ፣

## 5.3 ለመድሃኒት አገልግሎት

በዚህ ረገድ የወስጥ ገቢ በቅደሚያ ሊወል የሚገባው ማስረታዊ ለሆኑ የሕክምና መድሃኒቶች ግዢ ነው፡፡ በማስረታዊ የሕክምና መድሃኒቶችን ግዢ ከሚፈፀም በተጨማሪ የጤና ተቋማት የመድሃኒት ግዢ በሚያቅዱበት ወቅት የጤና ተቋሙ በሚገኝበት ጂኦግራፊያዊ አካባቢ ከሚኖረው የበሽታዎች ስርጭትና ጫና አኳያም ትኩረት ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ወጡታማ የሆነ የመድሃኒት አገልግሎት ለማስጠት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ማከያዎችን ያሟላ ሆኖ በወስጥ ገቢ ሊገዙ ከሚገባቸው ዝርዝሮች ወስጥ ቀጥሎ የተጠቀሱት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

1. የማስረታዊ መድሃኒቶች ግዢ
2. በጤና ሴክተር ልማት ፕሮግራም ወስጥ የቅድሚያ ትኩረት ለተሰጣቸው መድሃኒቶች ማለትም ለእናቶችና ሕፃናት ጤና ሕክምና የሚያገለግሉ፣ ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር ተጓዳኝ ለሆኑ በሽታዎች ለወባ፣ለሣንባ ነቀርሳ በተለይም እነዚህ የተዘረዘሩ መድሃኒቶች በዕርዳታ ሰጪዎች የማይሟሉ ከሆነ፣
3. ለአካባቢው ሕብረተሰብ ስለአጠቃላይ ጤናና የመድሃኒቶች አጠቃቀም ለማዘጋጅ የሥልጠና ፅሁፎች ዝግጅትና ግዢ፣
4. ለመድሃኒት ክምችት አገልግሎት የሚውሉ ዕቃዎችና መሳሪያዎችን ለማሟላት፣ በተጨማሪም ከ3 ወር ያልበለጠ የአገር ወስጥ ስልጠናዎችን ወጪ ለመሸፈን (ስልጠናዎቹ ከመድሃኒት አያያዝና አስተዳደር ጋር የተገናኙ መሆን ይኖርባቸዋል)፡፡

## 5.4 ሕክምና ነክ ያልሆኑ ዕቃዎችን ለማሟላት

የጤና ተቋማት የወስጥ ገቢ እንደየደረጃቸው አስፈላጊ ለሆኑ ሕክምና ነክ ላልሆኑ ዕቃዎችና መሳሪያዎች መግዣ ሊወል ይችላል፡፡ ከነዚህ ሕክምና ነክ ካልሆኑ ዕቃዎችና መሳሪያዎች ወስጥ የሚከተሉት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

1. የፋክስ፣ የስልክና ኢንተርኔት አገልግሎት ለሚሰጡ የመገናኛ ዕቃዎችና መሳሪያዎች፣
2. የእጥበት ማሽን/ዝርዝሩ በዕዝል ላይ ተመልክቷል/
3. አቅምን ያገናዘበ የልብስ መተኮሻ ማሽን፣
4. የዋጋ ተመጣጣኝነትን ከግምት ወስጥ ያስገባ በኤሌክትሪክ ወይም በፔዳል የሚሰሩ የልብስ ስፌት ዕቃዎች፣
5. እንደኮምፒዩተርና ተጓዳኝ መሳሪያዎች ለመሳሰሉ የጤና ተቋሙን የሚረጃ ማስረትና ፍላጎት ለማሻሻል ለሚውሉ አገልግሎቶች፣
6. ለተለያዩ ሚረጃዎች ምዝገባ የሚያገለግሉ ካርዶችን ለማስተም፣

7. ለጤና አገልግሎት ጥራት መሻሻል የሚያገለግሉ ሌሎች ማሽቸውም ሕክምና ነክ ያልሆኑ ዕቃዎች፣

## 5.5 የቢሮ ቋሚ ዕቃዎችና አቅርቦቶች

የወስጥ ገቢ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት የቢሮ ወስጥ ማልገያ ዕቃዎችና አቅርቦቶች ማሟያ ሊወል ይችላል፡፡ ሆኖም እነዚህ ዕቃዎች ገደብና መመዘኛ ለበጀላቸው ይገባል፣

1. ኮምፒዮተር እና ማዙሚያ መሳሪያዎች፣
2. የወረቀት ማባዣ ማሽን፣
3. የፎቶ ኮፒ ማሽን፣
4. የሂሣብ መደመሪያ ማሽን፣
5. ፋይል ካቢኔት፣
6. ካዝና
7. ስካነር፣ስልክ ኢንተርኔት
8. የጽሕፈት መሣሪያዎችና ቀለሞች፣
9. ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የቢሮ ዕቃዎችና  አቅርቦቶች፣

## 5.6 ቋሚ የቢሮ ማሽሪያዎች

አስፈላጊ ሲሆን በተቋሙ አመራር አካል ውሣኔ የወስጥ ገቢ ለቢሮ ቋሚ መሳሪያዎች ግዢ ሊወል ይችላል፡፡

## 5.7 መሰረተ ልማቶች

የጤና ተቋማት የወስጥ ገቢ የተለያዩ መሰረተ ልማቶችን ለማሟላት፣
ለመገንባትና ለማጠገን ተግባር እንደሚውል የሚጠበቅ ሲሆን፡ ከነዚህ ወስጥ የሚከተሉት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

### ሀ. ለወሃ አቅርቦት

1. ተቋሙን ከወሃ መስመር ጋር ለማገናኘት የሚደረግ ቧንቧ ማዘርጋት፣
2. ለወሃ ማከማቻ ጋን ግዢና ግንባታ፣
3. የተቋሙ ወሃ ምንጭ ከንፁህ የቧንቧ መስመር ካልሆነ ወሃን ለማከም፣
4. የወሃ ጉድጓዶችን ለመቆፈር፣
5. ወሃን ለማከም ለሚውሉ ኬሚካሎች ግዢ፣

### ለ. ለኤሌክትሪክ ኃይል

1. የጤና ተቋሙን በአካባቢው ካለ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ለማገናኘት፣

2. የኤሌክትሪክ ኃይል አመንጪ ጀነሬተር ለመግዛትና ጥገና ፣

3. ለሌሎች አማራጭ ኤሌክትሪክ ኃይል ምንጮች አቅርቦት ለምሳሌ በፀሐይ ኃይል የሚሰራ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ

**ሐ. የተቋማ ሕንፃዎች ለማሻሻል**

በዚህ ረገድ የተቋማ አገልግሎት ለማሻሻል ለሚደረጉ ግንባታዎችና ለጥገና ሥራ ለሆኑ ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩ ተግባራት ሊውል ይችላል

1. ለተማላላሽ ታካሚዎች የሚውሉ ተጨማሪ ክፍሎች ግንባታ፣
2. ለወሊድና የቀዶ ጥገና ክፍሎች፣
3. ለአስተዳደር ክፍሎች፣
4. ለተኝቶ ታካሚዎች የሚውሉ ተጨማሪ ክፍሎች ግንባታ፣
5. ለድጋፍ ሰጪ አገልግሎት፣
6. ለዲያግኖስቲክ አገልግሎት፣
7. ለመድሃኒት ማከማቻ መጋዘኖች፣
8. ለግቢ አትክልቶች ማስዋቢያ፣

**መ. ለትራንስፖርት አገልግሎት**

1. ለአምቡላንሶች፣ ለሞተር ሳይክሎችና ለተራ ብስክሌቶች ግዢና ጥገና፣
2. የቤንዚን ወይም ናፍጣ ዘይቶች ግዢ ወጪ ለመሸፈን፣

## 5.8 ለአካባቢ ንፅህና

1. ጊዜያዊ ልዩ ልዩ ቆሻሻዎችን ለማከማቸት የሚውሉ ዕቃዎች ግዢ
2. የተለያዩ የፕላስቲክ ከረጢቶች፣
3. በሽታ አምጪ የሆኑ ተዋሲያንን ለመግደል የሚረዱ ኬሚካሎች ግዢ
4. ለደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻዎች እንዲሁም ከወላድ ክፍሎች የዕንግዴ ልጅ ማስወገጃ የሚውሉ ጋኖችና ጉድጓዶች ግንባታ፣
5. የቆሻሻ መጣያ ጉድጓዶችንና ጋኖችን ለማጽዳት የሚውሉ ክፍያዎች፣
6. ለአናጺነት፣ ግንባታና የቧንቧ ሥራ የሚውሉ ዕቃዎችና መሳሪያዎች ግዢ
7. የተቋማ ክፍሎች ለማጽዳት አስፈላጊ ለሆኑ እንደመጥረጊያ፣ መወልወያና የተለያዩ የጽዳት ኬሚካሎች ግዢ

9. ለኢንሲኒሬተር ግንባታና ጥገና ሥራ፣

## 5.9 ለጤና ማኅበረሰብ፣ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር ስራዎች

የጤና ተቋማት የወስጥ ገቢ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት የጤና ትምህርትንና የበሽታ መከላከል ተግባራትን ለማጠናከር ሥራዎች ሊውል ይችላል፣

1. ለህብረተሰቡ የጤና ትምህርት ለማስፋፋት የሚረዱ ዕቃዎችና መሳሪያዎች ግዢ
2. ህብረተሰቡን በዋና ዋና የጤና ችግሮች ዙሪያ በስፋት ለማስተማርና ለሚዲያ፣ ለትምህርትና ትምህርታዊ ቅስቀሳ የሚውሉ መሳሪያዎችን ለመግዛት፣
3. ለእናቶችና ሕፃናት እንዲሁም ሥነ-ምግብ ክሊኒኮች ወስጥ በግብዓትነት የሚገለግሉ መሳሪያዎች ለማሟላት፣
4. ለቤተሰብ ጤና ክብካቤ አስፈላጊ የሆኑ መድሃኒቶች፣ እንደ ቫይታሚን ኤ ያሉ እናቶችና ሕጻናት በተጨማሪ ምግብነት የሚገለግሉና ሌሎችም እንደ አይረንና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች በመንግሥት ወይም መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚቀርቡ ከሆነ፣

## 5.10 ለሥልጠናና ለምርምር ወጪዎች

1. ማስረታዊ ለሆኑ ለተቋሙ ሠራተኞች ለሚሰጡ አቅም ግንባታ ሥልጠናና ተከታታይ ትምህርት የሚገለግሉ ዕቃዎችና መሳሪያዎች ግዢ /ዝርዝሩ በዕዝል----ላይ ተመልክቷል/፣
2. ከሶስት ወር ላልበለጡ የአገር ወስጥ ሥልጠናዎች ወጪዎችን ለመሸፈን፣

## 5.11 የሚዲያና የሜጅመንት ሥርዓትን ለማሻሻል

1. ለታካሚዎች መመዝገቢያ ካርድ ሕትመት፣
2. የተቋም ሚዲያ ለማዛዝ የተዘጋጁ ሶፍትዌሮች መግዣ
3. ለመድኃኒትና ለሕክምና መሳሪያዎች ለላብራቶሪ፣ ለፋይናንስ ግዢና ንብረት አስተዳደርና፣ የሰው ኃይል አስተዳደርን ለማገዝ የተዘጋጁ የኮምፒዩተር ሥርዓትን ለማቋቋም

## 5.12 ሥራ ማስኬጃ ወጪዎች

1. ለቢሮ እቃወች ለህክምና መሳሪያዎችና መድሃኒቶች አቅርቦት ግዢ ለሚደረግ ጉዞ እና የትራንስፖርት ወጪ ለመሸፈን፣
2. ለተቋሙ የሚገዙ ዕቃዎችና መሳሪያዎች የመጫና የማራገፍያ ጉልበት ወጪ
3. ለተሽከርካሪዎችና ጀነሬተር የሚውል ነዳጅ ግዢ
4. የተቋሙ ወሃ ምንጭ ቧንቧ ካልሆነ ለወሃ ሕክምና የሚውሉ ኬሚካሎችን ለመግዛት፣
5. የጤና ተቋሙ ለተጠቀመባቸው የወሃ፣ ኤሌክትሪክና ስልክ ፍጆታ ወጪዎችና ማከል ወጪዎች ሊወል ይችላል፡፡

## 5.13 የቅብብሎሽ ሥርዓትን ለማሻሻል

- ለአምቡላንስ፣

5.14 የሠራተኞችን ችሎታና የስራ ተነሳሽነት ለማዳበር የሚረዱ እና ገንዘብና ከገንዘብ ወጪ ያሉ ማበረታቻ፣ የሀገር ወስጥ የአጭር ጊዜ ስልጠና፣ የልምድ ልወውጥና የመሳሰሉትን፣

5.15 በተቋሙ ወስጥ ለሚሰጡ የተለያዩ ህክምናዎች ለምሳሌ ለአይንና ቀዶ ጥገና በተጋባዥነት ለሚመጡ ስፔሻሊስት ሐኪሞች ክፍያ ሊወል ይችላል፣ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ክፍያዎች አስፈላጊነታቸው በተቋሙ አመራር ታይቶ ሲጸድቅ ብቻ ተፈጻሚ የሚሆኑ ናቸው

## ክፍል ስድስት

## 6. ክትትልና ግምገማ

በጤና አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር ሥርዓት ላይ ክትትል እንደሚደረገው በተመሳሳይ ሚልኩ የጤና ተቋማት በወስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ሥርዓታቸው ላይ ገቢውን የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በክትትልና ግምገማ የሚገኙ ሚጃዎች በጤና ተቋሙ አመራር አካላት የጤና ጣቢያ ከፍተኛ አመራር የሆስፒታል ቦርድ/ ለሚወሰኑት ወሳኔዎች በአስረጂነት ከማጠቀማቸው በላይ የሚጠሩ የአፈጻጸም ማነናከሎችን ለሚገምና የተቋሙ አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት እንዲሻሻል እገዛ ያደርጋል፡፡ ክትትልና ግምገማ ለተቋሙ የወስጥ ውሣኔ አሰጣጥ በግብዓትነት ከማገልገሉም በተጨሪ በተቋሙ አገልግሎት አሰጣጥ ለማጎልትና ለሕዝብ ያለ ተጠያቂነትን ለሚረጋገጥ ጠቃሚ የሆነ ማሪያ ነው፡፡

ለመተግበር ቀላል የሆነ ክትትልና ግምገማ ሥርዓት በተቋማዊ ወስጥ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ ከወስጥ ገቢ የሚገኝ ሀብት በአግባቡ ወጪ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል ከመሆኑም በላይ አጠቃላይ በተቋሙ ወስጥ የሚከናወኑ ተግባራት በወቅቱ፣ በበቂ መጠን፣ በጥራት መከናወናቸውን፤ በተጨማሪም ለአገልግሎት የሚያስፈልጉ ዕቃዎች ግዢ በአግባቡና በጥንቃቄ መከናወኑን ለመከታተል ያስችላል፡፡

ለመተግበር ቀላል የሆነ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት በሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ፣ አመልካቾችን በማዘጋጀትና የክትትል ግቦችን በመጣል የአገልግሎት ጥራት ለማሻሻል ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን ደረጃ ማውቅና የአፈጻጸም ችግሮችን ማየት ይጠይቃል፡፡

ቁልፍ የአፈጻጸም ደረጃ አመልካቾችን በማየትና የክትትል ግቦችን በጤና ተቋሙ ሜኔጅመንት፣ ከፍተኛ አመራሮች /ቦርዶች/ እንዲሁም ሕግ አወጪ አካላት ውሣኔ መሰረት የወስጥ ገቢ አጠቃቀም ላይ ክትትል ማድረግ የሚከተሉትን ተግባራት ያካትታል፡፡

- በፊዚካልና በፋይናንስ ረገድ የተከናወኑ ተግባራትን ከዕቅድ ጋር በማነጻጸር ቋሚ የሆኑ ወቅታዊ /ወርሃዊ፣የሩብ አመት፣ የግማሽ አመትና ዓመታዊ/ የሥራ አፈጻጸም ግምገማ ማድረግ፣
- በዕቅድ ዘመኑ ካጸደቀው ከወስጥ ገቢ ስራ ላይ የዋለውን መጠን /መቶኛ/ ለማወቅ /ወርሃዊ፣የሩብ አመት፣ የግማሽ አመትና ዓመታዊ ግምገማዎችን ማድረግ፣
- በዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥና አጠቃቀም ላይ ክትትል በማድረግ
  - በዕቅድ ዘመኑ የተገዙ ዕቃዎችና አገልግሎቶች መጠንን ለይቶ ማወቅ፣
  - የተገዙ ዕቃዎችና አገልግሎቶች በጥቅም ላይ መዋል አለመዋላቸውን ማረጋገጥ፣
  - የተገዙ ዕቃዎችና አገልግሎት አጠቃቀም ከአገልግሎት ጥራት ጋር ባለው ግንኙነት ላይ አስተያየቶችን ማቅረብ፣

## 6.1 የአፈጻጸም ክትትል

### 6.1.1 መደበኛ የሆነ የክትትል ሥርዓት እንዲኖር በማድረግ

- በወስጥ ገቢ አጠቃቀም ዙሪያ በሚመለከታቸው ሁሉም የሥራ ክፍሎችና ግለሰቦች ዘንድ ኃላፊነትና ተጠያቂነት እንዲጠናከር ማድረግ፣
- በጤና ተቋሙ ወስጥ በፋይናንስና የቴክኒክ ዘርፎች ኃላፊነትን የሚወስዱ ባለሙያዎችን በመመደብ በወስጥ ገቢ አጠቃቀምና እንዲሁም ከቴክኒክ የሥራ ክፍሎች በአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት፣ በተጠቃሚዎች ቁጥር፣ በጊዜ አጠቃቀም በዕቃዎችና አገልግሎቶች ወቅታዊ አቀራረብ ወዘተ መደበኛ ሪፖርት ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ማድረግ፣
- በግዢ የቀረቡ ዕቃዎች አገልግሎቶች አጠቃቀም ረገድ ወርሃዊ፣ የሩብ፣ የግማሽ አመትና ዓመታዊ የሆኑ መደበኛ ሪፖርቶች እንዲቀርቡ ማድረግ፣

- ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀምን ለማካት የሚያስችሉ አማካኞች በበቂ ሁኔታ በሚደበኛው የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ ወስጥ እንዲካተቱ ማድረግ፣
- የወስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀምን ለማካት በሚዘጋጀው ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ ላይ የሚታዩ የአፈጻጸም ችግሮችንና የመፍትሄ ሃሳቦችን ለማጠቆም የሚያስችል ክፍል እንዲኖረው ማድረግ፣

### 6.1.2 በክትትል የሚገኙ መረጃዎችን ለወቅታዊ ውሳኔ ማጠቀም

- በተቋሙ ክትትልአማካይነት የሚገኙ መረጃዎች ለተቋሙ ሜጅመንትና ከፍተኛ አመራር /ቦርድ ቀርቦ በችግሮች ላይ ወይይት መደረጉን ሚረጋገጥ ተገቢ ይሆናል፣
- በክትትል ወቅት በተለያዩ የአፈጻጸም ችግሮች ላይ የተቋሙ ሜጅመንትና አመራሩ በአግባቡ የተማከቷቸው መሆኑ መከታተልና ሚረጋገጥ፣

## 6.2 ግምገማ

የጤና ተቋማት /ጤና ጣቢያዎችና ሆስፒታሎች/ ከወስጥ ገቢ የሰበሰቡትን ገቢ አስቀርተው እንዲጠቀሙበት ማድረግ፣ በኢትዮጲያ የጤና ሥርዓት ወስጥ በቅርብ ጊዜ የተጀመረ ተግባር ነው፡፡ ሆኖም መደበኛ በሆነ መልኩ ዳሰሳ በማድረግ በማምገም የአጠቃቀሙ ሁኔታ የጤና ክብካቤ ጥራትን በማሻሻል ረገድ ካለው ፋይዳ አንፃር ሊታይ ይገባዋል፡፡

የጤና ተቋማት የወስጥ ገቢያቸወን አስቀርተው እንዲጠቀሙ ቢደረግም አጠቃቀሙ ተጠያቂነትን ያገናዘበ እንዲሆን የማድረግ ከፍተኛ ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው፡፡ ስለሆነም አጠቃቀሙ ተጠያቂነትንና ግልፅነትን የተላበሰ መሆኑን ለሚረጋገጥ ከሚጠቀሙ መንገዶች ዋንኛው ወቅታዊ የሆነ የአፈፃፀም ግምገማ ማድረግ ነው፡፡

የወስጥ ገቢ አጠቃቀም ለተቋሙ አገልግሎት ጥራት መሻሻል ተገቢወን አስተዋፅኦ ማድረጉን ለማምገም ሲባል ቀጥሎ የተጠቀሱ ዋና ዋና ጉዳዮችን ሚፈፀም ይገባል፡፡

- ጠቅላላ ከተሰበሰበው ገቢ ወስጥ ጸድቆ በተፈቀደው ዝርዝር መሠረት ጥቅም ላይ የዋለወን መጠን በመቶኛ ማወቅ፣
- የወስጥ ገቢወን በማጠቀም በተደረጉ የዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዢና አቅርቦቶች ምክንያት ጥራት መሻሻሉንና አለመሻሻሉን ማወቅ፣
- ወጪ የተፈቀደባቸው ዝርዝሮች /positive lists/ ተከትሎ ከአጠቃላይ በጀት ወጪ የተደረገ ገንዘብ በመቶኛ ማወቅ፣
- የጤና ክብካቤ ገንዘብ ማገኛ ስልት ትግበራና በጤና ክብካቤ ጥራት ለውጥ ምክንያት በተቋሙ ሠራተኞች እርካታ፣ ተነሳሽነትና አፈጻጸም የታየ ለውጥ ማምገም

- በተቋሙ ውስጥ በተደረገ ጠፍ ነክ አፈጻጸም ጥራት ለውጥ ምክንያት በተገልጋዮች ዕርካታ ማሳኪያ የተገኙ ለውጦችን ማየት፣
    - የተደረገው እንቅስቃሴ የሕግ ማዕቀፍን ተከትሎ መፈጸሙን መከታተል፣
    - ለጥራት መሻሻል ወደፊት የሚገበሩ እንቅስቃሴዎችን ማየት፣
    - ዓመታዊ የአፈጻጸም ግምገማዎችን ማድረግና በየሁለት አመቱ ደግሞ ዝርዝር የሆነ ግምገማ ማካሄድ፣

# 7. አባሪዎች

## 7.1 ዕዝል አንድ

### 1. በጤና ሴክተር የልማት ፕሮግራም መመዘኛ ማስፈርት ማሰረት ለጤና ጣቢያዎች የሚያስፈልጉ የሕክምና ማልገያ መሳሪያዎች ዝርዝር

### 1.1 የሚያስፈልጉ የላቦራቶሪ ማልገያ መሳሪያዎች ዝርዝር

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | ብዛት | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | የደም መመርመሪያ | 1 | |
| 2 | የኬሚስትሪ መመርመሪያ ማሽን | 1 | |
| 3 | የግሉኮስ ማከያ | 2 | |
| 4 | ኤሌክትሮኒክስ ሴንትራፊዩጅ | 3 | |
| 5 | ማይክሮስኮፕ | 4 | |
| 6 | የኢ.ኤስ.አር ማከያ | 15 | |
| 7 | የነጭ ደም ሴል ቁጥር ማከያ | 1 | |
| 8 | እስትራላይዘር | 1 | |
| 9 | በእጅ የሚሰራ ሴንትራፊጅ | 1 | |
| 10 | እስቶፕዋች | 2 | |
| 11 | የቀይ ደ/ሴል ማከያ | 1 | |
| 12 | የላቦራቶሪ ምርመራ ብርጭቆ | 3 ጥቅል | |
| 13 | የእስቴን ማዘጋጃ ራክ (Staining rack) | 3 ጥቅል | |
| 14 | የተሟላ የቢሮ ላቦራቶሬ ማከያ | | |
| 15 | ማቀዝቀዣ/ትልቁ/ | 1 | |

### 1.2 የሚያስፈልጉ የምርመራ ዕቃዎች

| ተ.ቁ | መግለጫ | ብዛት | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | የተሟላ የዓይን መመርመሪያ | 1 በጥቅል | |
| 2 | የምርመራ መዶሻ (percussion Hammer) | 1 በነጠላ | |
| 3 | የአፍንጫ መመርመሪያ ስፔኩለም | 2 በነጠላ | |
| 4 | ፊቶትስኮፕ (Fetoscope) | 1 በነጠላ | |
| 5 | የዓይን እይታ መመርመሪያ ( Visual Acuity chart) | 1 በነጠላ | |

## 1.3 የሚያስፈልጉ የማዋለጃ ማልገያ መሳሪያዎች ዝርዝር

| ተ.ቁ | ማዋለጃ ክፍል | ብዛት | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | የማዋለጃ አልጋ | 2 | |
| 2 | ዲጅታል የሽል የልብ ትርታ መመርመሪያ ማሽን | 1 | |
| 3 | ማዛጫያ | 3 | |
| 4 | ምድጃ | 1 | |
| 5 | ሕፃን ማዋለጃ ቫክዩም | 3 | |
| 6 | ከአፍንጫ ፈሳሽ መምጠጫ /Suction apparatus/ | 2 | |
| 7 | የሕፃናት ሚዛን | 2 | |
| 8 | የማዋለጃ ሙሉ ዕቃ /Delivery set / | 10 | |
| 9 | የእንፋሎት መቀቀያ (Steam sterilizer) | 2 | |
| 10 | የምርመራ አምፑል/ Examination light/ | 2 | |
| 11 | የሕፃናት ትንፋሽ መቋረጥ ማከሚያ ዕቃ/ Infant | 5 | |
| 12 | ጠቅ መላቢያ | 5 | |
| 13 | የሞተ ፅንስ ጭንቅላት ማዋለጃ ዕቃ | 1 | |
| 14 | የሕክምና መሳሪያዎች ማስቀመጫ ሣጥን/ Instrument cabinet/ | 2 | |
| 15 | ፈሳሽ መምጠጫ /Aspirator/ | 2 | |
| 16 | ኦክሲጂን መስጫ መቆጣጠሪያ ሲሊንደር (oxygen cylinder | 2 | |
| 18 | ሰሃን ከነ ማስቀመጫ | 2 | |
| 19 | የሽል እስቴትስኮፕ (fethoscope ) | 6 | |
| 20 | የአይቢ ማቆሚያ (IV stand) | 5 | |
| 21 | የደም ግፊት መለኪያ ከነ ስቴትስኮፕ | 4 | |
| 22 | ተሽከርካሪ ጎማ ያለው ጠረጴዛ (Trolly) | 6 | |
| 23 | የሕፃን አልጋ | 2 | |
| 24 | ሰሃን | 4 | |
| 25 | የመቀስ ማስቀመጫ | 4 | |
| 26 | የማዋለጃ መቀስ | 3 | |
| 27 | ማቀዝቀዥ | 2 | |

| ተ.ቁ | ማዋለጃ ክፍል መሳሪያዎች | መለኪያ | ብዛት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | እስፖንጅ ፎርሴብስ | በነጠላ | 2 | |
| 2 | ቆዳ ማነጠቂያ ፎርሴብስ Dissecting forceps | " | 1 | |
| 3 | ደም ሥር መቆንጠጫ ፎርሴብስ/Pean artery forceps/ | " | 4 | |
| 4 | እምብርት መቆንጠጫ/Umbilical cord compreser forceps/ | " | 1 | |
| 5 | የእፒዞቶሚ መቀስ | " | 1 | |
| 6 | የስፌት መርፌ መያዥ(needle holder) | " | 2 | |
| 7 | የሴት ሽንት መሸኛ ቱቦ (Female catheter) | " | 1 | |
| 8 | የማጠቢያ ሰሀን / Bowl wash/ | " | 1 | |
| 9 | የፈሳሽ መቀበያ ሰሀን | " | 1 | |
| 10 | መቁረጫ መቀስ / Straight steach scissor/ | " | 1 | |
| 11 | የደም ሥር መቆንጠጫ /Kocher's artery forceps/ | " | 2 | |

## 1.4 የሚያስፈልጉ የማስተኛ ቀዶ-ጥገና የሕክምና መሳሪያዎች

| ተ.ቁ | የማስተኛ ቀዶ-ጥገና የሕክምና መሳሪያዎች | መለኪያ | ብዛት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ባለ140 ሚ.ሜ አርተሪ ፎርሴፕስ | በቁጥር | 2 | |
| 2 | ባለ115ሚ.ሜ ዳይሴክቲንግ ፎርሴፕስ | " | 1 | |
| 3 | ባለ145ሚ.ሜ ዳይሴክቲንግ ፎርሴፕስ | " | 1 | |
| 4 | ስፓንጅ ሆልድንግ " | " | 2 | |
| 5 | ባለ 3 ስካልፐ ሀንድል | " | 1 | |
| 6 | ባለ 4 ስካልፐ ሀንድል | " | 1 | |
| 7 | ባለ140 ሚ.ሜ ሜዩ ከርቭድ ሲዘር | " | 1 | |
| 8 | ባለ145 ሚ.ሜ ስትሬት ሲዘር | " | 1 | |
| 9 | ባለ140 ሚ.ሜ ክሊፕ ታወል | " | 4 | |
| 10 | ባለ4x5 ጥርስ ቲሹ ፎርሴፕስ | " | 2 | |
| 11 | ባለ165ሚ.ሜ ኒድል ሆልደር | " | 2 | |
| 12 | ባለ203 ሚ.ሜ ኘሮብ ባለ ጋይድ | በቁጥር | 1 | |
| 13 | ባለ170ሚ.ሜ ትንሽና መካከለኛ ኩዩሬት | " | 1 | |
| 14 | ባለ140ሚ.ሜ 4x5 ጥርስ ርቲራክተር | በጥንድ | 1 | |
| 15 | ሲንክ ሁክ ግልስ /Sink hook Gilles/ | በቁጥር | 2 | |
| ተ.ቁ | ማስተኛ ቀዶ-ጥገና የሕክምና መሳሪያዎች | መለኪያ | ብዛት | ምርመራ |
| 16 | ባለ150 ሚ.ሜ ሀለት ጠርዝ ርቲራክተር | በጥንድ | 2 | |
| 17 | ርትራክተር 23x7 ትንሹ | " | 2 | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 18 | ባለ145ሚ.ሜ ሞስኪይቶ አ/ፎርሴፕስ ስትሬት | በቁጥር | 5 | |
| 19 | ባለ145ሚ.ሜ ሞስኪቶ አ/ፎርሴፕስ ከርቭድ | በቁጥር | 5 | |
| 20 | ባለጥርስ ቲካፕ ፎርስፕስ | " | 1 | |
| 21 | ጥርስ የሌለው ፎርሴፕስ | " | 1 | |
| 22 | ባለ100 ሲሲ ጋሊ ፖት | በነጠላ | 2 | |
| 23 | ባለ18 ሳ.ሜ ሲቭዲ ኮከርስ አርተር ፎርሴፕስ | " | 2 | |

## 1.5 የሚያስፈልጉ የቀዶ ጥገና /Operation / እና ስትራላይዜሽን መልገያ መሳሪያዎች ዝርዝር

| ተ.ቁ | የኦ.አር እና የስትራላይዜሽን ክፍል መልገያ መሳሪያዎች | ብዛት | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | በእጅ የሚሰራ የቀዶ ጥገና ጠረጴዛ /Manually operating Operation table | 1 | |
| 2 | ተንቀሳቃሽ የቀዶ ጥገና መብራት | 1 | |
| 3 | የፈሳሽ ማማጠጫ ማሽን | 1 | |
| 4 | እስትራላይዝንግ ማሽን /Dry Oven Sterilizing Machine/ | 1 | |
| 5 | የእንፋሎት መቀቀያ steam sterilizer | 2 | |
| 6 | የደም ግፊት መለኪያ | 2 | |
| 7 | የልብ ትርታ ማዳመጫ | 2 | |
| 8 | እንስትሩሜንት ቲሮሊ | 2 | |
| 9 | እንስትሩሜንት ቲሬይ | 15 | ትልቁ |
| 10 | እንስትሩሜንት ቲሬይ | 15 | መካከለኛ |
| 11 | ስትራላይዜሽን ዳራም | 5 | ትልቁ |
| 12 | ስትራላይዜሽን ዳራም | 5 | መካከለኛ |
| 13 | ስትራላይዜሽን ዳራም | 5 | ትንሹ |
| 14 | የፕላስቲክ ባልዲ | 5 | |
| 15 | ሰሀን ማስቀመጫ ቋም/ Bowl stand/ | 3 | |
| ተ.ቁ | የኦ.አር እና የስትራላይዜሽን ክፍል መልገያ መሳሪያዎች | ብዛት | ምርመራ |
| 16 | ማስተኛ የቀዶ ጥገና ዕቃ | 15 | ሰንጠረዥ1.4 ይመለከቱ |
| 17 | ግሉኮስ መስቀያ IV stand | 2 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 18 | የቀዶ ጥገና ወንበር | 4 | |
| 19 | የስትራላይዜሽን ዳራም ማስቀመጫ | 5 | |
| 20 | መቆጣጠሪያ ያለው ኦክስጂን ሲሊንዳር | 1 | |
| 21 | እንስትሩሜንት ካቢኔት | 5 | |
| 22 | ፊልተር ትሬይ | 2 | |
| 23 | ስትሬቸር | 2 | |
| 24 | የተሟላ የጥርስ ማንቀያ ዕቃ | 3 | ሰንጠረዥ1.6 ይመልከቱ |

## 1.6 የጥርስ ማንቀያ መሳሪያዎች

| ተ.ቁ | የጥርስ ማንቀያ መሳሪያዎች | መለኪያ | ብዛት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የትንሹ መንጋጋ ጥርስ ማንቀያ ፎርሴፕስ | በነጠላ | 1 | |
| 2 | የላይኛው መንጋጋ ጥርስ ማንቀያ ፎርሴፕስ | " | 1 | |
| 3 | የክራንች ጥርስ ማንቀያ ፎርሴፕስ | " | 1 | |
| 4 | ባለ150 ሚ.ሜ/6ኢንች ደርቢ ፔሪ ስኬለር ዊንግ ሼፕ | " | 2 | |
| 5 | ባለ150 ሚ.ሜ/6ኤንች ስኬለር ዴንታል ሐንድፔኒ "2" ቁጥር ማለያ ያለው | " | 2 | |
| 6 | ባለ150 ሚ.ሜ/6ኤንች ስኬለር ዴንታ ሐንድ ፔኒ"0"ቁጥር ማለያ ያለው | " | 2 | |
| 7 | ሰሀን ባለ 300 ሲሲ | " | 1 | |
| 8 | ኪዲኒ ዲሽ ባለ600 ሲሲ | " | 1 | |

## 1.7 የሕሙማን ምርመራ ክፍል የሕክምና መሳሪያዎች

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | ቁጥር |
|---|---|---|
| 1 | የደም ግፊት መለኪያ | 1 |
| 2 | የምርመራ አልጋ | 1 |
| 3 | ኤግዛም ላይት | 1 |
| 4 | የአዋቂ ሚዛን | 1 |
| 5 | የልብ ትርታ ማዳመጫ | 1 |

| | | |
|---|---|---|
| 6 | ሙሉ የዲያግኖስቲክስ ሴት | 1 |
| 7 | ቴርሞ ሜትር | 1 |
| 8 | ሜትር | 1 |
| 9 | የዓይን ዕይታ ማለኪያ | 1 |
| 10 | የእጅ ባትሪ | 1 |
| 11 | የሕመማን ምርመራ ማለያ | 1 |
| 12 | ተሸከርካሪ ጠረጴዛ | 2 |

## 1.8 <u>የእናቶችና ሕፃናት የሕክምና ማልገያ መሳሪያዎች</u>

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | ቁጥር |
|---|---|---|
| 1 | የማህፀን መመርመሪያ ጠረጴዛ | 1 |
| 2 | የልብ ትርታ ማዳመጫ | 1 |
| 3 | የሽል ልብ ትርታ ማዳመጫ | 1 |
| 4 | የደም ግፊት ማለኪያ | 1 |
| 5 | የእጅ ባትሪ | 1 |
| 6 | ቴርሞ ሜትር | 1 |
| 7 | የነጭ ጋዝ ምድጃ | 1 |
| 8 | እንስራ/ክዳን ያለው/ | 2 |
| 9 | የቲሮሊ እንስትሩሜንት | 1 |
| 10 | ፈሳሽ ማለኪያ ያለው ጆግ | 2 |
| 11 | ኤግዛም ላይት | 1 |
| 12 | ሜትር | 1 |
| 13 | ስቲም ኢንስትሩሜንት እስትራላይዘር/ፕሬዥር ኩክር/ steam sterilizer | 1 |
| 14 | መግቢያና መውጫ ሰዓት መቆጣጠሪያ | 1 |
| 15 | የአዋቂ ሚዛን | 1 |
| 16 | የእናቶችና ሕፃናት ዲያግኖስቲክስ ኪት | 1 |
| 17 | የሕፃናት ሚዛን | 1 |
| 18 | መቀስና የመቀስ ማስቀመጫ | 1 |

## 1.9 <u>የሕክምና መሳሪያዎች</u>

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | ቁጥር |
|---|---|---|

| | | |
|---|---|---|
| 1 | ግሉኮስ ማስቀያ IV stand | 1 |
| 2 | የሕክምና መሳሪያዎች ማስቀመጫ ሰሀን | 1 |
| 3 | የምርመራ አልጋ | 1 |
| 4 | ተሽከርካሪ ጠረጴዛ | 1 |
| 5 | አውቶክሊብ/ጀርም መግደያ/ | 1 |
| 6 | ሁለት እጀታ ያለው እስክሪን | 1 |
| 7 | የኦክስጂን ስሊንደር የመቆጣጠሪያ ጌጅ | 2 |
| 8 | የቁስል ሜጅኛ መሳሪያ | 5 |
| 9 | የጥጥ ማያዣ ኩባያ | 1 |
| 10 | የእንፋሎት መቀቀያ ድራም | 2 |
| 11 | ጉድጓዳ ሳህን | 1 |
| 12 | ማቀዝቀኘ | 1 |
| 13 | መቀስ ማስቀመጫ | 1 |
| 14 | ስትሬቸር ባለጎማ | 1 |

## 1.10 የፋርማሲ እቃዎች

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | ቁጥር |
|---|---|---|
| 1 | መድኃኒት መቁጠሪያ ትሪ | 1 |
| 2 | የማለኪያ ስሊንደር | 2 |
| 3 | የማዝገ ሚዛን | 1 |
| 4 | ማቀዝቀዣ | 1 |
| 5 | ሁለገብ ትሮሊ | 1 |
| 6 | ማንኪያ | 2 |
| 7 | ውኃ ማጣሪያ | 1 |
| 8 | ፈሳሽ መለኪያ ጆግ | 1 |

## 1.11 የወንዶችና የሴቶች አልጋ ክፍል ዕቃዎች

### ሀ.ሴቶች/ወንዶች ተኝተው የሚታከሙበት ክፍል

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | ቁጥር |
|---|---|---|
| 1 | የሴቶች ሽንት መሸኛ ዕቃ Bed pan | 6 |
| 2 | ኪዲኒ ድሽ | 6 |
| 3 | የግሉኮስ ማስቀያ IV stand | 6 |
| 4 | የአከታ ማትፊያ ከባያ | 3 |
| 5 | ወንበር /ተሽከርካሪ/ | 1 |
| 6 | እስክሪን/ሕሙማን ማለያ/ | 1 |
| 7 | የሆድ ማጠቢያ ሰሀን enema can | 1 |
| 8 | የሕክምና መሳሪያዎች ማስቀመጫ ሰሀን | 3 |

## 1.12 የሕጻናት ዋርድ ማልገያ ዕቃዎች

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | ቁጥር |
|---|---|---|
| 1 | የሽንት መሸኛ ፖፖ | 2 |
| 2 | ኪዲኒ ድሽ | 1 |
| 3 | የግሉኮስ ማስቀያ | 1 |
| 4 | የአከታ ማትፊያ ከባያ | 3 |
| 5 | አልጋ | 3 |

## 7.2. ዕዝል ሁለት

### 2. ለሆስፒታሎች የሚያስፈልጉ የሕክምና ማልገያ መሳሪያዎች ዝርዝር

### 2.1 የራጅ ምርመራ የሕክምና መሣሪያዎች

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | ቁጥር |
|---|---|---|
| 1 | የተሟላ የራጅ ምርመራ ዩኒት | 1 |
| 2 | የጨለማ ክፍል ማልገያ መሣሪያ | 1 |
| 3 | የራጅ ምርመራ ካሴት | |
| 4 | የራጅ ምርመራ ማለያ መጋረጃ | |
| 5 | የራጅ ፊልም ማስቀያና ማድረቂያ | |
| 6 | ለጨለማ ክፍል ማጣጠሚያ ዕቃ | |
| 7 | የአቫሪ ራጅ ማንሻ የተሟላ ዕቃ | 3 |
| 8 | የራጅ ፊልም ማጠቢያ ማኮ ዕቃ | 1 |
| 9 | የራጅ ፊልም ማጠቢያና ማቆያ ክፍል | 1 |
| 10 | የራጅ ፊልም ማድረቂያ | 1 |
| 11 | ፊልም ማጠራቀሚያ ሣጥን | 1 |
| 12 | ሰዓት መቆጣጠሪያ | 1 |
| 13 | የራጅ ፊልም መመርመሪያ | 1 |

### 2.2. የላቦራቶሪ ህክምና መሳሪያዎች

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | ቁጥር |
|---|---|---|
| 1 | ውኃ ማነከሪያ | 1 |
| 2 | ማይክሮስኮፕ | 3 |
| 3 | ሆሞሳይቶ ሜትር | 10 |
| 4 | ደም ማስቀመጫ ማቅዝቀዣ | 1 |
| 5 | አናላይቲካል ባላንስ | 1 |
| 6 | ኤሌክትሪካል ሴንትሪፊዮጅ | 2 |
| 7 | ሄማቶክሪት ሴንትሪፊዮጅ | 1 |
| 8 | የስላይድ ማስቀመጫ | 10 |
| 9 | እስትራላይዘር | 1 |
| 10 | የነጭ ደም ሴል መቁጠሪያ | 1 |
| 11 | አልኮል ማቃጠያ | 4 |

| | | |
|---|---|---|
| 12 | ጊዜ መቆጣጠሪያ | 2 |
| 13 | የተሟላ የላቦራቶሪ መሞርመሪያ | 3 |
| 14 | የኤስ.አር ራክ | 2 |
| 15 | እስፖኪቶፎቶ ሜትር | 1 |
| 16 | እስቴይንግ ራክ | 2 |

## 2.3 የማህፀን ምርመራ ህክምና መሳሪያዎች

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | ቁጥር |
|---|---|---|
| 1 | ቫክዩም ኤክስትራክተር ማጉዋል | 1 |
| 2 | የተሟላ ማዋለጃ ዕቃ | 6 |
| 3 | ማህፀን ማፅጊያ ሙሉ ዕቃ | 2 |
| 4 | የማህፀን ቀንድ መቋጠሪያ ሙሉ ዕቃ | 2 |
| 5 | እስቴትስኮፕ | 2 |
| 6 | የኤልክትሪክ እስቶቭ | 2 |
| 7 | የደም ግፊት መለኪያ | 2 |
| 8 | የጨቅላ ሕጻን ሚዛን | 1 |
| 9 | የማዋለጃ አልጋ | 2 |
| 10 | የሽል ልብ ትርታ መለኪያ | 2 |
| 11 | ተንቀሳቃሽ የአይቪ ማስቀያ IV stand | 3 |
| 12 | የአዋቂ ፓፓ bed pan | 2 |
| 14 | ሳህን ባለ 5 ሊትር | |
| 15 | ኪዳኒ ዲሽ ባለ170 ሲሲ | 2 |
| 16 | የሕፃን ማጠቢያ | 1 |
| 17 | ባልዲ | 2 |
| 18 | የአዋቂ አልጋ | 8 |
| 19 | የሕፃን አልጋ | 5 |
| 20 | ፈሳሽ ማምጠጫ | 1 |
| 21 | የማዋለጃ መቀስ | 2 |
| 22 | የጨቅላ ሕፃን እንኩቤተር | 4 |
| 23 | ዝርግ ሰሀን | 4 |
| 24 | ቴርሞ ሜትር ክሊኒካል | 4 |
| 25 | ቴርሞ ሜትር ሬክታል | 4 |
| 26 | የሕፃን ትንፋሽ ማስተካከያ የተሟላ ዕቃ | 2 |

| | | |
|---|---|---|
| 27 | የማህፀን መመርመሪያ አልጋ | 3 |

## 2.4. የኦፕራሲዮን ሕክምና መሳሪያዎች /ለሁለት ክፍሎች/

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | ቁጥር |
|---|---|---|
| 1 | ማደንዘዣ | 2 |
| 2 | የቀዶ ጥገና ክፍል ማብሪያ አምፑሎች | 2 |
| 3 | ተንቀሳቃሽ የቀዶ ጥገና መብራት | 2 |
| 4 | ፈሳሽ መምጠጫ/ፖርቴብል/ | 1 |
| 5 | ሁለገብ የቀዶ ጥገና ጠረጴዛ | 2 |
| 6 | ኤሌክትሮ ቀዶ ጥገና ዩኒት | 2 |
| 7 | ሙሉ በሙሉ የተሟላ ከ/ቀ/ጥገና ዕቃ | 4 |
| 8 | ሙሉ በሙሉ የተሟላ መለ/ቀ/ጥገና ዕቃ | 4 |
| 9 | የኦክስጂን ታንክ Cylinder እና መቆጣጠሪያ | 4 |
| 10 | የተሟላ የማኅፀን ማጠቢያ ዕቃ | 2 |
| 11 | የማህፀን ቀዶ ጥገና ዕቃ | 4 |
| 12 | አይቪ ማስቀያ | |
| 13 | የቀዶ ጥገና ወንበር | 4 |
| 14 | መለስተኛ የዓይን ቀዶ ጥገና ዕቃ | 2 |
| 15 | የመታጠቢያ ሰሀን ከነመቆሚያ | 4 |
| 16 | ፈሳሽ መምጠጫ | 1 |
| 17 | የሕጻን ሚዛን | 1 |
| 18 | ሜዮ ቲሮሊ | 2 |
| 19 | ፊልተር ትሬይ | 3 |
| 20 | ሁለገብ ትሮሊ | 2 |
| 21 | ዝርግ ትሮሊ | 2 |
| 22 | ተኝቶ የሚታከም በሽተኛ | 2 |
| 23 | እስትራላይዘር ዳራም ስታንድ | 2 |
| 24 | የቁስል ማሸጊያ | 1 |
| 25 | የትንፋሽ መቋረጥ ማስተካከያ አምቡባግ | 2 |
| 26 | እስቴትስኮፕ | 1 |
| 27 | የደም ግፊት መለኪያ | 1 |
| 28 | የውኃ ማፍያ | |

| | | |
|---|---|---|
| 29 | ትራክዩስቶሚ ሴት | 2 |
| 30 | አምፒውቴሽን ሴት | 1 |
| 31 | የደረት ፈሳሽ ማስወገጃ ቱቦ | 5 |
| 32 | የደረት ፈሳሽ ማጠራቀሚያ ጠርሙስ ባለ1.5 ሊትር | 5 |

<u>መግለጫ</u>

- ከ/ቀ/ጥገና፡ ከፍተኛ ቀዶ ጥገና
- ማለስ/ቀ/ጥገና፡ ማለስተኛ ቀዶ ጥገና

## 2.5 <u>የእስትራላይዜሽን መገልገያ መሳሪያዎች</u>

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | ቁጥር |
|---|---|---|
| 1 | ሃይ ፕሬዥር እስትራላይዘር | 1 |
| 2 | ሃይ ፕሬዥር እስቲሞ እስትራላይዘር | 1 |
| 3 | እስትራላይዝንግ ቲሮሊ | 1 |
| 4 | ባለ25 ሊትር ዲስ እንፌክሽን ማጣሪያ ዕቃ | 2 |
| 5 | ባለ5ና ባለ15 ሊትር እስትራላይዘር ድራም | 20 |
| 6 | ፊልተር ቲሬይ | |
| 7 | እስትራላይዘር | 2 |
| 8 | እንስትሩሜንት እስትራላይዝንግ ቲሬይ | 2 |
| 9 | ባለ3 ሼልፍ ቲሮሊ | 1 |

## 2.6 <u>የተሟላሽ ሕክምና ምርመራ መሳሪያዎች</u>

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | ቁጥር |
|---|---|---|
| 1 | ስቴትስኮፕ | 2 |
| 2 | የደም ግፊት ማለኪያ | 2 |
| 3 | ክሊኒካል ቴርሞ ሜትር (digital thermometer) | 2 |
| 4 | ሬክታል ቴርሞ ሜትር | 2 |
| 5 | ኮምፕሊት ዲያግኖስትክ ሴት | 2 |
| 6 | የአዋቂ ሚዛን | 2 |
| 7 | የሕፃናት ሚዛን | 1 |
| 8 | ማቅዝቀዣ | 1 |

| | | |
|---|---|---|
| 9 | ባለሁለት ዝርግ ስክሪን | 3 |
| 10 | እንስትሩሜት ቲሮሊ | 2 |
| 11 | ፕላስቲካል ካፕ | 4 |
| 12 | ኤግዛምኔሽን ላይት | 2 |
| 13 | የአይቪ ማስቀያ IV stand | 2 |
| 14 | የተሟላ የጥርስ ማንቀያ ሴት | 4 |
| 15 | የምርመር አልጋ | 3 |
| 16 | ዝርግ ትሮሊ | 2 |
| 17 | አምባባግ ያለው ኦክስጂን ሲሊንደር | 2 |
| 18 | ድሬስንግ ሴት | 10 |
| 19 | እንስትሩሜት ትሪ | 2 |
| 20 | ሚይነር ኦፕሬሽን ቴብል ሙዋል | |
| 21 | ተንቀሳቃሽ የቀዶ ጥገና መብራት | 1 |
| 22 | ማስ/ቀዶጥገና የተሟላ ሴት | 4 |
| 23 | ግለቀሳ ማስቀያ ብረት | 4 |
| 24 | የማህፀን ማጠቢያ የተሟላ ዕቃ | 4 |
| 25 | እንስትሩሜት ቲሮሊ | 2 |
| 26 | የቀዶ ጥገና መቀመጫ ወንበር | 2 |
| 27 | ባለ350 ሚ.ሜ ፈሳሽ ማስቀያ ብረት | 1 |
| 28 | ተሽከርካሪ ወንበር | 1 |
| 29 | መቆንጠጫ መቀስ ከነ ማስቀመጫው | 4 |

## 2.7 የእናቶችና ሕፃናት የጤና ምርመራ መሳሪያዎች

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | ቁጥር |
|---|---|---|
| 1 | ሞባይል ኤግዛሜሽን ላይት | 1 |
| 2 | የምርመራ አልጋ | 1 |
| 3 | የልብ ትርታ ማዳመጫ | 1 |
| 4 | የደም ግፊት ማለኪያ | 1 |
| 5 | የአዋቂ ሚዛን | 1 |
| 6 | በባትሪ ድንጋይ የሚሰራ የእጅ ባትሪ | 2 |
| 7 | ክሊኒካል ቴርሞ ሜትር | 2 |
| 8 | ሬክታል ቴርሞ ሜትር | 2 |

| | | |
|---|---|---|
| 9 | ስክሪን ሁለት ተካፋች ያለው | 1 |
| 10 | ቤቢ ቦትል/ግላስ/ | 1 |
| 11 | የመማቢያ ማንኪያ | 2 |
| 12 | ባለ1000 ሲሲ ፈሳሽ ማለኪያ ጆግ | 2 |
| 13 | ባለ100 ሲ.ሲ የፕላስቲክ መቅጃ | 2 |
| 14 | ባለ 2 ሊትርና ባለ4 ሊትር ፈሳሽ የሚይዝ እንስራ | 2 |
| 15 | ባለ170 ሲ.ሲ ኪዲኒ ዲሽ | 2 |
| 16 | ባለ100 ሲ.ሲ ጥጥ ማስቀመጫ ኩባያ | 2 |
| 17 | ባለ3 መደርደሪያ ትሮሊ | 1 |
| 18 | የእናቶችና ሕፃናት ጤና መመርመሪያ መሣሪያ | 4 |
| 19 | ጠጅ ማጠቢያ | 2 |
| 20 | የሕፃናት ሚዛን | 1 |
| 21 | የኤሌክትሪክ ምድጃ | 1 |
| 22 | የሽል ልብ ትርታ ማዳመጫ | 1 |

## 2.8 የመድሃኒት ፋርማሲ ማልገያ መሳሪያዎች

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | ቁጥር |
|---|---|---|
| 1 | ክኒን መቁጠሪያ ቲሬይ | 1 |
| 2 | ሜዠሪንግ ሲሊንደር | 2 |
| 3 | ፕሪስክሪፕሽን ባላንስ | 1 |
| 4 | ማቀዝቀዥ | 1 |
| 5 | ሁለ ገብ ቲሮሊ | 1 |
| 6 | ማንኪያ | 2 |
| 7 | ወኃ ማጣሪያ | 1 |
| 8 | ፈሳሽ ማከኪያ ጆግ | 1 |

## 2.9 የሴቶችና የወንዶች ዋርድ ማልገያ መሳሪያዎች

**ለሴቶች ዋርድ**

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | ቁጥር |
|---|---|---|
| 1 | ባለ900 ሲ.ሲ ፓፓ የሴት ሽንት መሽኛ( bed pan) | 9 |
| 2 | ባለ170 ሲ.ሲ ኪዲኒ ዲሽ | 4 |
| 3 | አልጋ | 18 |
| 4 | አይቪ ማስቀያ | 9 |
| 5 | ባለ100 ሲ.ሲ አክታ መትፊያ | 18 |
| 6 | ባለጎማ ስትሬቸር (mobile strecher) | 1 |

**ለወንዶች ዋርድ**

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | ቁጥር |
|---|---|---|
| 1 | የወንዶች ሽንት መሽኛ (urinal) | 7 |
| 2 | ባለ170 ሲ.ሲ ኪዲኒ ዲሽ | 4 |
| 3 | አልጋ | 2 |
| 4 | አይቪ. ማስቀያ | 7 |
| 5 | አክታ መትፊያ ባለ100 ሲ.ሲ | 15 |
| 6 | ባለጎማ ስትሬቸር | 2 |

## 2.10 የሕፃናት ዋርድ ማልገያ መሳሪያዎች

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | ቁጥር |
|---|---|---|

| | | |
|---|---|---|
| 1 | ፓፓ | 7 |
| 2 | ባለ170 ሲ.ሲ ኪዳኒ ዲሽ | 4 |
| 3 | ግሉኮስ ማስቀያ | 7 |
| 4 | አልጋ | 15 |

## 2.11 የአይሶሌሽን ዋርድ ማልገያ መሳሪያዎች

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | ቁጥር |
|---|---|---|
| 1 | አልጋ | 2 |
| 2 | ፓፓ | 2 |
| 3 | አይቪ ማስቀያ | 2 |
| 4 | ባለ100 ሲ.ሲ ክዳን ያለው ኩባያ | 2 |
| 5 | ባለ170 ሲ.ሲ ኪዳኒ ዲሽ | 2 |

## 2.12 የነርሶች ቢሮ ማልገያ መሳሪያዎች

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | ቁጥር |
|---|---|---|
| 1 | እንስትሩሜንት ትሮሊ | **1** |
| 2 | ሜዲሲን ትሮሊ | **1** |
| 3 | የመድኃኒት ማስቀመጫ ካቢኔት | **1** |
| 4 | የምርመራ ዕቃ ማስቀመጫ ካቢኔት | **1** |
| 5 | የቁስል ማሸጊያ መሳሪያ | 10 |
| 6 | የአዋቂ ሚዛን | 1 |
| 7 | የሕፃናት ሚዛን | 1 |
| 8 | እኑስትሩሜንት ቲሬይ | 3 |
| 9 | ስክሪን ባለሁለት ተካፋች | 3 |
| 10 | የኤሌክትሪክ ምድጃ | 1 |
| 11 | ቴርሞ ሜትር | 2 |
| 12 | የልብ ትርታ ማዳመጫ | 2 |
| 13 | የደም ግፊት ማለኪያ | 2 |
| 14 | የሆድ ማጠቢያ | 2 |
| 15 | የእጅ ባትሪ | 2 |
| 16 | የኦክስጂን ሲሊንደር | 2 |
| 17 | ፈሳሽ ማምጠጫ ማሽን Suction machine | 1 |

## 7.3 ዕዝል ሶስት

### 3. የሥልጠና የገለፃ ማልገያ ማሳሪያዎች

### 3.1 ለጤና ጣቢያዎች

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት |
|---|---|
| 1 | ጥቁር ሰሌዳ |
| 2 | ፔፐ |
| 3 | ድምፅ ማጉያ |
| 4 | - የማነፀን አጥንቶች<br>- ሽል<br>- የእንግዴ ልጅ |
| 5 | ሥንጠረዦች<br>- ፊልፐ ቻርቶች<br>- የኤ.አር.አይ መመሪያዎች<br>- የተቅማጥ መመሪያዎች<br>- የቤተሰብ ዕቅድ መመሪያዎች<br>- የርግዝና መመርመሪያዎችና ስዕሎች<br>- የምግብ እጥረት መመርመሪያዎች<br>- የሰው ምስል<br>- የሰው መወለጃ አካል ምስሎች |
| 6 | የኦ.አር.ቲ ማሎ ዕቃ |
| 7 | የአዋቂ ሚዛን |
| 8 | የሕፃናት ሚዛን |
| 9 | የምግብ ማበሰያ ዕቃዎች |
| 10 | የማወለጃ ኪት |
| 11 | መጽሐፍትና መመርመሪያዎች |
| 12 | የሕፃናት ገላ ማጠቢያ ባዝ |
| 13 | ገንቦች |
| 14 | የጽሕፈት መሳሪያ |
| 15 | ወንበርና ጠረጴዛ |

### 3.2. ለሆስፒታል ማልገያ ዕቃዎች

| ተ.ቁ | የዕቃ ዓይነት |
|---|---|

| | |
|---|---|
| 1 | የስብሰባ ጠረጴዛ |
| 2 | የጥናት ጠረጴዛ |
| 3 | የተማሪ መቀመጫ ወንበር |
| 4 | የክንድ መደገፊያ ያለው ወንበር |
| 5 | ወንበር ከነጠረጴዛ |
| 6 | የጠዎሜ ሰሌዳ |
| 7 | የቁም ሣጥን |
| 8 | የመጽሐፍ መደርደሪያ |
| 9 | ፕሬድካል ስታንድ |